Language L.19

# AMHARIC

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام

Version Date: November 2025




Part of the

ISLAMIC e-LIBRARY

Learn more about Islam with our informative and educational materials, translated to over 50+ languages

@islamicicdxb

CONTENTS


ሰለ ኢሰላም አጭር ትውውቅ

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን)

መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው

የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢሰላም

ቁርኣን ለመላው የሰው ዘር የመጨረሻው ራዕይ

የህይወት አላማ ምንድን ነው?

ስለ ኢሰላም የተዛቡ ግንዛቤዎች

የሴቶች መብቶች በኢሰላም

የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር

ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢሰላም


# ሰለ ኢሰላም አጭር ትውውቅ

AMHARIC | (01/10) نبذة عن الإسلام | FREE COPY

ተግባራዊና ሚዛናዊ የአኗኗር ዘይቤ

ከአላህ ጋር ያለ የጠበቀና ቀጥተኛ ግንኙነት

ስለ አምላክ ትክክለኛና ግልጽ ግንዛቤ

ለሁሉም ዘመንና ቦታ የሚሆን መልእክት


جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES

Your Path To Peace..

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام

تصريح رقم:
(2017/139)

دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

www.islamicic.com

CONTENTS






# እስልምና ምንድን ነው?

እስልምና አንድ እውነተኛ አምላክን (በዐረብኛ "አላህ" ይባላል) ማመን፣ እርሱን ብቻ ማምለክ እና ነቢዩ ሙሐመድን (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) የመጨረሻ ነቢይ አድርጎ ማመን ነው።

ከእያንዳንዱ አራት ሰዎች አካባቢ አንዱ (23%) ሙስሊም ነው። ይህም በዓለም ላይ ከሁለት ቢሊዮን በላይ ሙስሊሞች አሉ ማለት ነው።

የእስልምና ተከታዮች "ሙስሊሞች" በመባል ይታወቃሉ። ከማንኛውም ዘር ወይም ብሄር ሊሆኑ ይችላሉ።

# እምነት እና ዐቂዳ

አላህ በምልክቶቹ አማካኝነት በእርሱ እንድናምን ይጋብዘናል። ይህንን እውቀት የኛ ኃላፊነት አካል አድርጎታል። ይህም የዚህ ዓለም ህይወት ፈተና ክፍል ነው። ትክክለኛ መመሪያ ከሌለ ግን ምንም ያህል መረጃ ቢኖር አንድን ሰው አማኝ ሊያደርገው አይችልም።

| ✓ | ✗ |
|---|---|
| ሚዛናዊነት እና ክፍት አእምሮ | ወደ ኢስላም እንዳይገቡ እንቅፋቶች እና የተሳሳቱ ግንዛቤዎች |
| ትህትና እና ቅንነት | ትዕቢት እና ኩራት |
| የመገኘታችንን ዓላማ ማሰብ | ቁሳዊው ዓለም ላይ ብቻ ማተኮር |
| የአላህ ምልክቶችን ማስተዋል | ሁሉንም ነገር ትርጉም የለሽ አድርጎ መካድ |

# የመጀመሪያው ምክንያት፡ የፍጥረተ ዓለሙ አጀማመር

በአላህ ለማመን የመጀመሪያው ሰበብ የፍጥረተ ዓለሙን (ዩኒቨርስ) መነሻ ከማሰብ ጋር የተያያዘ ነው።

**ፍጥረተ ዓለሙ እንዴት ወደ መኖር መጣ?**

- ✗ ከምንም መጣ? ከምንም፣ ምንም አይመጣም። ስለዚህ፣ በእርግጠኝነት ይሄ አይሆንም።
- ✗ ራሱን ፈጠረ? አይሆንም። ይህ ምክንያታዊ አይደለም። እናት እራሷን ወለደች እንደማለት ነው።
- ✗ ዘላለም የነበረ ነው? አይሆንም። ዘመናዊ ሳይንስ ፍጥረተ ዓለሙ ዝንታለማዊ እንዳልሆነ፣ ይልቁንም መጀመሪያ እንደነበረው ያረጋግጣል።
- ✓ እናስ ተፈጥሮ ነው? አዎ። ሙስሊሞች ፍጥረተ ዓለሙ የተፈጠረው ከዩኒቨርስ ውጭ በሆነ ነገር እንደሆነ ያምናሉ። ይህም ፈጣሪ አምላክ ነው።

## ነገር ግን አላህን ማን ፈጠረው?

አላህ አልተፈጠረም። እርሱ የቀደመው የሌለ የመጀመሪያ ነው። ከርሱ በኋላ ምንም የማይኖር የሆነ የመጨረሻ ነው። ይህም ከዩኒቨርስ እና ከሌሎች ፍጥረታት በተቃራኒ ማለት ነው።

CONTENTS





# ሁለተኛው ምክንያት፡ የፍጥረተ ዓለሙ ስርአት

በአላህ ለማመን ሌላው ቀላል ሰበብ የሚከተለውን አመክንዮ በመጠቀም የዩኒቨርሱን ስርአት ማሰላሰል ነው።

1.ማንኛውም ስርአት ያለው ነገር እውቀትን ያመለክታል።

2. የእኛ የፀሐይ ስርአት እጅግ በጣም ረቂቅ ነው። ውስብስብ በሆኑ ህጎች እና ስርዓቶች የሚመራ ነው።

3. በዩኒቨርሳችን ውስጥ ያለው ስርአት የፈጣሪን እውቀት ያመለክታል።

ብዙ የዩኒቨርሰ ገጽታዎች ለሕይወት ድጋፍ እንዲሰጥ ተደርጎ የተሰራ መሆኑን በግልጽ ያመለክታሉ። እነዚህ መለኪያዎች አሁን ካሉት በመጠኑም ቢሆን የተለዩ ቢሆኑ ኖሮ ሕይወት የማይቻል ነበር። ይህንን እውነታ ከሚያሳዩ ምሳሌዎች ውስጥ፦

- የኦዞን ሽፋን
- የምድር ቅርፊት ውፍረት
- በአየር ውስጥ ያለው የኦክስጂን መጠን
- ምድር ከፀሐይ ያላት ርቀት
- የፀሐይ፣ የምድር እና የጨረቃ አንፃራዊ መጠን

በጣም ሰፊና ውስብስብ የሆነ ዩኒቨርስ ያለ ዕቅድና ትኩረት በአጋጣሚ ሊፈጠር ይችላልን? እስልምና ሳይንሳዊ ምርምርን እና ማሰላሰልን እንደሚያበረታታ ልብ ሊባል ይገባል። ሳይንስ አላህ በፍጥረቱ ውስጥ ያስቀመጣቸውን የሚታዩ ምልክቶች ለማሰስ ይረዳል። ይህም አንድ ሰው የአላህ ችሎታ እና ጥበብ የላቀ እንደሆነ ይበልጥ እንዲገነዘብ ያግዘዋል ማለት ነው።

# ሦስተኛው ሰበብ ራዕይ - ቁርኣን

ቁርኣን በአላህ መኖር ላይ ጠንካራ ማስረጃ ነው። በአቀራረቡ፣ በጥበቡ፣ በመመሪያው፣ በንግግራዊ ምጥቀቱ እና ከአንባቢው ጋር በሚኖረው ልዩ መስተጋብር ወደር የለሽ ነው።

- ስህተቶች ወይም ተቃርኖዎች የሉትም።
- ስለ አላህ ትክክለኛ እና ግልጽ መግለጫ ይዟል።
- የዐረብኛ ቋንቋ ውበቱ ጫፍ የደረሰ ነው።
- ለነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) የተሰጠ ነው። እርሳቸውም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ነበሩ።
- ለ1400 ዓመታት ያህል ተጠብቆ ቆይቷል።አልተለወጠም
- ስለ ሰው ባህሪ ጥልቅ ግንዛቤዎች አሉት።
- በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች በቃላቸው ሸምድደውታል።
- በዚያን ጊዜ ሰዎች የማያውቋቸውን ሳይንሳዊ እውነታዎች ይዟል።

**አላህ እንዲህ ብሏል፦**

“በምድርም ውስጥ ለሚያረጋግጡ ሰዎች ምልክቶች አልሉ። በእራሳችሁም ውስጥ (ምልክቶች አልሉ)። አይመለከቱምን?”

ሱረቱል ዛሪያት፡ 20 - 21

CONTENTS






# አላህ ማን ነው?

ከእስልምና ታላላቅ ውበቶች ውስጥ አንዱ የአላህን ፍፁምነት፣ ታላቅነት እና አንድነት ያለ ምንም ድርድር ማመን ነው።

- አላህ አንድ እና ብቸኛ ነው፣ አጋር የለውም፣ ተጋሪ የለውም፣ ልጅም የለውም።
- አላህ (ክብር ይገባውና) ሁሉም አምልኮ የሚገባው ነው፣ በቀጥታ እና በብቸኝነት፣ ያለ አማላጆች።
- አላህ ፍጹም ነው፣ ምንም ጉድለት ወይም ድክመት የለበትም።
- አላህ እጅግ አዛኝ ነው። እኛ ፍጹም እንዳልሆንን እና ኃጢአቶችን እንደምንሰራ ያውቃል። ሆኖም ቁልፉ ነገር ስህተቶቻችንን ሁልጊዜ አምኖ መቀበል እና ከልብ ምህረትን መጠየቅ ነው።
- አላህ በፍጥረቱ ላይ አይሰፍርም። እንዲሁም ማንም በአምላካዊ መገለጫዎቹ አይጋራውም።

በእስልምና የአምላክን ፅንሰ-ሀሳብ ለመረዳት ሲሞከር፣ ስለ ኢየሱስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ማንነት የተለመዱ የተሳሳቱ አመለካከቶች እና ስሬ ሙግቶች ሰላሉ የሳቸውን ቦታ መወያየት አስፈላጊ ነው።

በእስልምና ኢየሱስን (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ከአላህ የተላኩ የተከበሩ ነቢይ እና መልእክተኛ እንደሆኑ እናምናለን። ሆኖም ግን ሙስሊሞች እርሳቸውን አያመልኩም። ምክንያቱም አምልኮ ኢየሱስን ጨምሮ ሁሉንም ፍጥረት የፈጠረ ለሆነው ለአላህ ብቻ የሚገባ ነውና። ስለዚህ ኢየሱስን (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) አላህ ነው፣ ወይም የአላህ ልጅ ነው፣ ወይም ከሥላሴዎች አንድ አካል ነው ብሎ ማመን በእስልምና ስለ አላህ ካሉ ግልጽ ትምህርቶች ጋር ይቃረናል።

**ኢየሱስ አላህ ከሆኑ፣ ለማን ነበር የሚፀልዩት?**

በክርስትና ትምህርቶች ውስጥ ኢየሱስ ከአላህ የተለዩ አካል እንደሆኑ አድርገው የሚናገሩባቸው እና የሚያሳዩባቸው በርካታ ምሳሌዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ወደ አላህ ይጸልዩ ነበሩ።

**አላህ እንዴት ፍጹም የሆነ እና ፍጹም ያልሆነ ሊሆን ይችላል?**

ኢየሱስ የተወለዱ ናቸው። ምግብ የሚበሉ፣ እንቅልፍ የሚወስዳቸው ነበሩ። እውቀታቸውም የተገደበ ነበር። እነዚህ ሁሉ ለአላህ የማይገቡ መገለጫዎች ናቸው።

አላህ በፍፁም ሙሉእነት የተገለጸ ነው። ሰው ግን በተቃራኒው ፍጹም አይደለም። ለድክመትም የተጋለጠ ነው።

**“የአላህ ልጅ” የሚለው ቃል በተጨባጭ ምን ማለት ነው?**

“የአላህ ልጅ” የሚለው ቃል በቀደሙ ጽሑፋዊ ቋንቋዎች ብዙ ሰዎችን ከሚያመለክት “ጻድቅ” ሰው ጋር በተያያዘ ዘይቤያዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ውሏል። እንጂ ለኢየሱስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ብቻ የተገደበ አይደለም። አላህ ምንም ዓይነት ቁሳዊም ይሁን እውነተኛ ልጅ ከመውለድ የጠራ ነው።

## አላህ ሁሉንም ነገር ማድረግ ከቻለ፣ እንዴት ሰው ሊሆን አይችልም?

አላህ ሁልጊዜ የፍጹምነት መገለጫዎችን ይጠብቃል። ፍፁምነቱን የሚቃረን ወይም እነዚያን ፍፁምነቶች የሚጎዳ ምንም ነገር አያደርግም። እንደ ትርጓሜ የሚወሰደው “አምላክ” አምላካዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን አያደርግም። ስለዚህ፣ አምላክ ሰው ከሆነ እና የሰውን መገለጫ ከወሰደ፣ የግድ በዚያን ጊዜ አምላክ አይሆንም ማለት ነው።

CONTENTS






**(ኖሕ)፣ ኢብራሂም (አብርሃም)፣ ሙሳ (ሙሴ)፣ ዒሳ (ኢየሱስ)፣ ሙሐመድ እና ሌሎችም (ውዳሴና ሰላም በእነርሱ ላይ ይሁን)**

- የአንድ አምላክ ፅንሰ-ሀሳብን ያረጋግጣሉ።
- ሐሰተኛ አማልክትን እና እምነቶችን ይቃወማሉ።
- አላህን እንዴት ማምለክ እንደሚቻል ያብራራሉ።
- የበጎ ሰራ እና መልካም ስነምግባር ምሳሌ ይሆናሉ።
- የታዛዥነትን ሽልማት (ጀነት) ይገልፃሉ።
- ከአመፀኛነት ቅጣት (ጀሀነም) ያስጠነቅቃሉ።

አላህ ነቢያትን በዘመናት ሁሉ ለሁሉም ሕዝቦች በተመሳሳይ ታላቅ መልእክት ልኳል። አንድ አምላክን እንዲያመልኩ። ሙስሊሞች ሁሉንም ነቢያት ቢወዱም እና ቢያከብሩም፣ እነርሱን አያመልኩም ወይም መለኮትነትን አይሰጧቸውም። ምክንያቱም መለኮትነት የአላህ ብቻ መብት ነውና።

## የሕይወት ዓላማ

ጥበበኛው አላህ ያለምንም ዓላማ ወይም መሰረታዊ ስሜቶቻችንን እና ምኞቶቻችንን ለማርካት ብቻ አልፈጠረንም። ይልቁንም፣ ከፍ ያለ ዓላማ አለን - አላህን ብቻ ማመን እና ማምለክ፣ እንዲሁም በእርሱ ህግ መሰረት መኖር። ይህ መመሪያ በሁሉም ዘርፎች ደስተኛ እና የተሳካ ህይወት ለመኖር ሰበብ ነው።

ፍፃሜ ከሌለው የአላህ ጥበብ ውስጥ አንዱ የፈጠረን እና እርሱን ለማወቅ፣ የህይወታችንን ልምድ ለመውሰድ እና የራሳችንን ምርጫ ለማድረግ እድል የሰጠን መሆኑ ነው።

እስልምና ጠቅላይ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ ነው። ሙስሊሞችን ሚዛናዊነትን፣ መልካም ስነምግባርን እና በህብረተሰብ ውስጥ አዎንታዊ መሆንን ያስተምራል። በእስልምና ውስጥ የአምልኮ ፅንሰ-ሀሳብ በሶላት እና ወደ አላህ መማፀን ላይ የተወሰነ አይደለም። ነገር ግን አላህን የሚያስደስት ማንኛውንም ተግባር የሚያካትት ሁሉን አቀፍ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። በዚህ ላይ ከሚጠቀሱ ምሳሌዎች መካከል፡-

- ሐላል መተዳደሪያ መፈለግ፣
- በደልን መቃወም፣
- ወላጅ አልባዎችን መንከባከብ፣
- አካባቢን መንከባከብ፣
- ትዕግሰት እና ትህትና፣
- ህብረተሰብን መጥቀም፣
- ወላጆችን ማክበር፣
- ከፍትህ ጎን መቆም፣
- ለጎረቤቶች መልካም መዋል፣
- አላህን መፍራት፣
- ቤተሰብን መደገፍ፣
- እውነት መናገር

የአምልኮ ተግባራት አላህን ለማስደሰት ቅን እሳቤ ያስፈልጋቸዋል። እንዲሁም በእስላማዊ መመሪያዎች መሰረት በትክክል መፈጸም አለባቸው።

CONTENTS






# እስልምና ስለ ... ምን ይላል?

**ሴቶች:** ሴቶች በእስልምና ከፍተኛ ክብር አላቸው። በፍቅር፣ በክብር እና በአክብሮት መታየት አለባቸው። እነርሱ የወንዶች እህቶች ወይም ክፋዮች ናቸው። ስለሆነም ይህ እውነታ በጭቆና ወይም በግፍ ሊለወጥ አይችልም።

**ሽብርተኝነት:** እስልምና ሃይማኖታቸው ምንም ይሁን ምን ንጹሐን ሰዎችን ማጥቃትን ይከለክላል። በእስልምና ውስጥ መዋጋት የተፈቀደውም ለክቡር እና ህጋዊ ዓላማዎች ብቻ ነው። እርሱም ማህበረሰብን ለመጠበቅ፣ የፍትሕ መጓደልን ለመከላከል እና ፍትህን ለማጠናከር ነው።

**ሐላል ምግቦች:** ሙስሊሞች እንዲመገቡ የተፈቀደላቸው ሐላል ምግቦችን ሲሆን እነሱም የታወቁ እንስሳት ስጋዎችንና ዶሮዎችን ያካትታሉ። እነዚህም ሰብአዊነት ባለው መንገድ መታረድ አለባቸው። ይህም ስቃይን በመቀነስ ሲሆን በእርድ ጊዜ የአላህን ስም ማውሳት ግድ ይላል።

**ዝግመተ ለውጥ:** አላህ የመጀመሪያውን ሰው ማለትም አደምን (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) በፍፁም መልኩ ነው የፈጠራቸው። እንጂ ደረጃ በደረጃ “ከዝንጀሮዎች” አላዳበራቸውም። ይህ እውነታ (የአደም አፈጣጠር) ቀጥተኛ በሆነ ሳይንስ ሊረጋገጥም ሆነ ሊስተባበል አይችልም። ምክንያቱም ልዩ ታሪካዊ ክስተት (ተአምር) ስለነበር። ስለዚህም ምልከታን መሰረት ባደረገው የሳይንስ ምርምር ስር የሚታይ አይደለም።

## የሙስሊም የህይወት እይታ

- በአላህ ምህረት ላይ ተስፋ በመጣል እና የእርሱን ቅጣት በመፍራት መካከል ሚዛንን መጠበቅ።
- የከበረ ዓላማ አለኝ።
- መልካም ነገር ሲከሰት አመስጋኝ እሆናለሁ። መጥፎ ነገር ሲከሰት ደግሞ ታጋሽ እሆናለሁ።
- ይህ ህይወት ፈተና ነው። እና አላህ የምሰራውን ሁሉ ያያል።
- እምነቴን በአላህ ላይ እጥላለሁ። ምንም ነገር በእርሱ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አይከሰትም።
- ያለኝ ሁሉ ከአላህ የተሰጡኝ በረከቶች ናቸው።
- ሙስሊም ያልሆኑ አካላትን አላህ እንዲመራቸው እውነተኛ ተስፋና ትኩረት እሰንቃለሁ።
- አቅሜ በሚችለው ላይ ትኩረት አደርጋለሁ። ከዚያ በኋላ የተቻለኝን ጥረት ማድረግ።
- ወደ አላህ እመለሳለሁ። ለድርጊቶቼም እጠየቃለሁ።

CONTENTS

ስለ ኢስላም አጭር ትውውቅ
ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን)
መሲሑ ያመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው
የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም
ቁርኣን
የህይወት አላማ ምንድን ነው?
ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች
የሴቶች መብቶች በኢስላም
የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር
ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም

# ነብዩ ሙሐመድ

## (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን)

AMHARIC | (02/10) | النبي محمد عليه الصلاة والسلام | FREE COPY

እኚህን ሰው ሊያውቁ ይገባል!
ከእሳቸው የሕይወት ታሪክ ዋና ዋና ነጥቦችን ይወቁ።

جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae
الإمارات
THE EMIRATES
Your Path To Peace..
مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام
تصريح رقم:
(2017/139)
دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department
www.islamicic.com

CONTENTS





# ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ማን ናቸው?

ሙስሊሞች ነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) አላህ ሰዎችን ወደ አንድ አምላክ አምልኮ እንዲጠሩ የላካቸው ረጅም የነቢያት ሰንሰለት ውስጥ የመጨረሻው ክፍል እንደሆኑ ያምናሉ። ይህ ሰንሰለት እንደ አደም፣ ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ኢስማዒል፣ ኢስሓቅ፣ የዕቁብ፣ ዩሱፍ፣ ሙሳ፣ ዳውድ፣ ሱለይማን እና ዒሳ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ያሉ ነቢያትን ያጠቃልላል።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ።”
>
> ቁርኣን 33:21

ሙስሊሞች አላህ ለሙሳ ኦሪትን አውርዶላቸዋል ብለው ያምናሉ። ይህም የሰዎች እጅ ገብቶበት ከመበረዙ በፊት የነበረውን መለኮታዊ ራዕይ ለማለት ነው። እንዲሁም ለዒሳ ወንጌልን አውርዶላቸዋል ብለው ያምናሉ። ይህም የሰዎች እጅ ገብቶበት ከመበረዙ በፊት የነበረውን መለኮታዊ ራዕይ ለማለት ነው። በተመሳሳይ ለነቢዩ ሙሐመድም (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ቁርኣንን አውርዶላቸዋል ብለው ያምናሉ። ይህም ለሰዎች የተወረደላቸውን ግልጽ ለማድረግ እና ምናልባትም አላህን እንዲፈሩ ለማስታወስ ነው።

የመልዕክተኛው ባለቤት የምዕመናን እናት ዓኢሻ ስለ ባህሪያቸው ተጠይቃ የሠጠችው መልስ “በመሬት ላይ የሚራመድ ቁርኣን ነበሩ" የሚል

ነበር። (አሕመድ ዘግበውታል።)

ይህ ማለት በዕለታዊ የህይወት ውጣ ውረዶች ውስጥ የቁርኣንን አስተምህሮት ተግባራዊ ያደርጉ ነበር ማለት ነው። መልዕክተኛው (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) የቁርኣንን የላቁ አስተምህሮቶች ወደ ተግባር እንዴት እንደቀየሩ ከብዙ በጥቂቱ ለመመልከት እንሞክር።

## የእዝነት መልእክተኛ

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ለሰዎች ጥሪ ሲያደርጉ ወደ ሰግደት፣ ጾምና ምጽዋት ብቻ አልነበረም። ይልቁንም፣ እርሳቸው (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) አንድ ሰው በአላህ ላይ ያለው እምነቱ ከሌሎች ጋር በሚኖረው መልካም ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር እንዳለበት ያስተምሯቸው ነበር። ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "ከእናንተ በላጫችሁ በሥነ ምግባሩ ምርጡ ነው።" (ቡኻሪይ 6035)

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።"
>
> ቁርኣን 21:107

እምነት የእንደበት ምስክርነት ብቻ አይደለም። በልብ የሰፈረው እምነት በተግባርም መረጋገጥ ይኖርበታል። በርካታ የመልዕከተኛው ምክሮች እምነት ከተግባር ጋር ያለውን ትስስር ግልጽ አድርገው አስቀምጠዋል። ከእነዚህም መካከል፣ ለምሳሌ፣ የሚከተለው ንግግራቸው ይገኝበታል፦ ”በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ጎረቤቱን አያስቸግር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ እንግዳውን ያክብር፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምን ይናገር ወይንም ዝም ይበል።” (ቡኻሪይ 6018)

የመጨረሻው መልእክተኛ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ሰዎችን

CONTENTS




እርሰ በርሳቸው መተዛዘን እና መከባበር እንዲኖራቸው አስተምረዋል። እርሳቸው (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "የማያዝን አላህ አያዝንለትም።" (ቡኻሪይ 5997)

በሌላ ነብያዊ ሐዲሰ፤ አንዳንድ ባልደረቦቻቸው አላህ በጣኦታዊያን ላይ ቅጣቱን እንዲያወርድ ዱዓ ያደርጉ ዘንድ ጥያቄ ማቅረባቸው ተወሰቷል። መልዕክተኛው ይህን ጥያቄ ለመቀበል ፍቃደኛ አልነበሩም። የሰጡት ምላሽ “ተራጋሚ ሆኜ አልተላኩም፤ የተላኩት ለእዝነት ነው” የሚል ነበር። (ሙስሊም 2599)

# ይቅር ባዩ ነብይ

ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ከሰዎች ሁሉ ይቅር ባይነታቸው የላቀ፣ እና ልባቸውም እጅግ ንፁህ ነበር። ማንም ሰው ቢያስቀይማቸው፣ ይቅር ይሉት ነበር። የአንድ ሰው ማስቀየም በጨመረ ቁጥር፣ የነቢዩ ትዕግስት ይጨምር ነበር። በተለይ ደግሞ ስልጣን በእጃቸው ሲሆን እና ሰዎች ለእርሳቸው ሲታዘዙ፣ እጅግ በጣም ታጋሽና ይቅር ባይ ነበሩ።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "ይቅርታም ያድርጉ። (ጥፋተኞቹን) ይለፉም። አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን? አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።" ቁርኣን 24:22

የነብዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ይቅር ባይነት የአንድ ሰሞን ግዜያዊ መገለጫ አልነበረም። በሁሉም አስቸጋሪ እና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አብሯቸው ዘልቋል። ብዙ በደሎች ቢፈራረቁባቸውም ይቅርታ አድራጊነታቸውን የሚፈታተኑ አልነበሩም። በተከበረው ቁርኣን ላይ የሰፈረውን መልዕክት በተጨባጭ ተግብረዋል፦

**"ገር ፀባይን ያዝ። በመልካምም እዘዝ። ባለጌዎቹንም ተዋቸው።"**
**ቁርኣን 7:199**

# እኩልነት

በሚከተሉት ሐዲሶች ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) የሰው ልጆችን በአላህ ዘንድ እንዴት እኩል እንደሆኑ ያስተምራሉ።



የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው።" ቁርኣን 49:13

እሳቸው (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ “የሁላችሁም አባት አደም ነው። አደም (የተፈጠረው) ከአፈር ነው። (በዘሩ ወይም በቆዳው ቀለም ምክንያት) ዐረብ የሆነው ዐረብ ባልሆነው ላይ፣ ጥቁሩ በነጩ ላይ ብልጫ የለውም። አላህን በመፍራት ቢሆን እንጂ።” (አሕመድ 23489)

በተጨማሪም (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ “አላህ ወደ መልካችሁ እና ገንዘቦቻችሁ አይመለከትም። ነገር ግን ወደ ልባችሁና ተግባራችሁ ይመለከታል።” (ሙስሊም 2564)


ከባልደረቦቻቸው መካከል አንዱ “የጥቁር ሴት” ልጅ በማለት ተገቢ ባለሆነ መልኩ ሌላውን ሰው ሲጠራ ተሠማ። የአላህ መልዕክተኛ በጣም ተቆጡ። “በእናቱ (የቆዳ ቀለም) ልታነውረው ሞከርክን? አንተ በርግጥ መሐይምነት በውስጥህ ያለብህ ሰው ነህ" በማለት ወረፋት። (ቡኻሪይ 30)


CONTENTS











# መጥፎን በመልካም የሚመልስ ነብይ

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "መልካሚቱና ክፉይቱም (ጸባይ) አይስተካከሉም። በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ጸባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር። ያን ጊዜ ያ ባንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይሆናል።"
>
> ቁርኣን 41:34

መጥፎን ተግባር በመጥፎ አለመመለስ የመልዕክተኛው መገለጫ ነበር። “የአላህ መልዕክተኛ መጥፎን በመጥፎ፣ ክፋትን በክፋት አይመልሱም ነበር። ይልቁንም ይቅር ባይ ነበሩ።” (ቡኻሪይ 4838)

የነቢያት መደምደሚያ የሆኑት (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ሲገለጹ እንዲህ ተብሏል፦ "ክፉን በክፉ አይመልሰም ነበር። ነገር ግን ይቅር ይልና ቾል ይል ነበር።" (ቡኻሪይ 4838)። በማንኛውም በሚፈፀምባቸው ጥቃት ወይም በማንነታቸው ላይ በሚደርስባቸው መተላለፍም የሚይዙት አመለካከት እንዲሁ ነበር።

ኢስላማዊ የታሪክ ድርሳናት፤ ታላቁ ነብይ ሙሐመድ የበደሏቸውን ሊበቀሉ የሚችሉባቸው ብዙ አጋጣሚዎች እንደነበሩና ሆኖም መበቀል እየቻሉ ይቅር ማለታቸውን በሚያስረዱ በርካታ ክስተቶች ታጭቀዋል።

አስቸጋሪና አስጨናቂ የህይወት ምዕራፎችን በጠንካራ ትዕግስት መጋፈጥ እንደሚያስፈልግ አስተምረዋል። “ጠንካራ ሠው በትግል የሚያሸንፍ አይደለም። ጠንካራ ሰው በቁጣ ወቅት እራሱን የሚቆጣጠር ነው” በማለት ምክር ሰጥተዋል። (ቡኻሪይ 6114)

እርግጥ ነው ትዕግስትና መቻቻል መላበስ ማለት አንድ ሙስሊም ለራሱ የሚሠጠውን ግምትና ክብር አሉታዊ እያደርገውም። ጥቃት ቢፈፀምበትም በዝምታ ይመልከት ማለትም አይደለም። በደልን ከራስ ላይ የመከላከል መብትን ኢስላም ያከብራል። በይቅርታ ማለፍን ግን ያበረታታል። ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "ጠላትን መገናኘት አትመኙ። ከአላህ ደህንነትን ለምኑ። ከእነርሱ ጋር ከተገናኛችሁ ግን ታገሱ።" (ቡኻሪይ፡ 2966)

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "ከአላህም በሆነች ችሮታ ለዘብክላቸው። ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በሆንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር።"
>
> ቁርኣን 3:159

## ድርቅና የማያውቀው ጸባየ ለስላሳ

አነሰ ኢብን ማሊክ ለ10 ዓመታት ከመልዕክተኛው ጋር በቅርብ አብሮነት ያገለገሉ እድለኛ ወጣት ነበሩ። አነሰ ስለ ባህሪያቸው እንዲህ ሲሉ ይናገራሉ፦ “በፍፁም አንድ ነገር ካደረግኩ በኋላ ለምን ይህን አደረግክ ብለው ወቀሳ ሰንዝረውብኝ አያውቁም፤ ያልሰራሁት ነገር ኖሮም (በወቀሳ) ለምን ይህን ነገር አልሠራህም ብለውኝ አያውቁም።” አህመድ 12784 ዘግበውታል። አንድ ሰው የመልዕክተኛውን ክብር ዝቅ ለማድረግ ሞከረ። ባለቤታቸው ዓኢሻ ተቆጣች።

እርሳቸው ግን እንድትረጋጋ መከሯት። "ዓኢሻ ሆይ ተረጋጊ። አላህ ሩህሩህ ነው፤ በሁሉም ነገሮች ላይ ለስላሳነትን ይወዳል" ሲሉ ገሠጿት። (ቡኻሪይ፡ 6024)

በተጨማሪም እንዲህ ብለዋል፦ “ማንኛውም ነገር ውስጥ እዝነት ሲኖር ውበትን ያላብሰዋል። ከምንም ነገር ላይ ሲነሳ ደግሞ ያጠለሸዋል።” (ሙስሊም 2594)

CONTENTS





# መተናነስ

የአላህ መልዕክተኛ ከኩራት የፀዳ ሰብዕና ነበራቸው። ሲገቡ በደረሱበት ክፍት ቦታ ይቀመጣሉ። ሰዎች ለርሳቸው ክብር ሲሉ ከመቀመጫቸው እንዳይነሱ ዘወትር ይከለክላሉ። ከባልደረቦቻቸው ልዩ የሚያደርጋቸው ልብስ አይለብሱም። ከችግረኛ ድሆች እንዲሁም እድሜያቸው ከገፋ ሽማግሌዎች ጋር ቆይታ ያደርጋሉ። ባሎቻቸው የሞቱባቸው ረዳት አልባ ሴቶች ድጋፍ እንዲያገኙ ጥረት ያደርጉ ነበር። ከሌሎች ተለይተው መታየትን ስለማይፈልጉ በሰዎች መካከል ሲሆኑ ቀድሞ የማያውቃቸው ሰው አይለያቸዉም ነበር።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "የአልረሕማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚሄዱት፣ ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው።"
>
> ቁርኣን 25:63

ለሶሀቦቻቸው ከኩራት ስለመጽዳትና ራስን ዝቅ ስለማድረግ አስተምረዋል። (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ባልደረቦቻቸውን እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ " **'ከኩራት በመራቅ ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ አንዳችሁ በሌላው ላይ ራሱን የበላይ ለማድረግ ትምክህት አይገባው። አንዳችሁ በሌላው ላይ ወሰን አይለፍ' የሚል መልዕክት አላህ አውርዶልኛል።"** (አቡ ዳውድ 4895)

መተናነሳቸውን ከሚያሳዩ ነገሮች ውስጥ አንዱ ከአላህ ውጭ እንዳይመለኩ መስጋታቸው ነው። በዚህም የተነሳ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

**"ክርስቲያኖች የመርየም ልጅ ዒሳን ከፍ ከፍ በማድረግ (ወሰን እንዳለፉት) እኔንም ከፍ በማድረግ (ወሰን አትለፉ) እኔ የአላህ ባሪያ ነኝና 'የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ' ስትሉ ጥሩኝ።"** (ቡኻሪይ: 3445)

# ተምሳሌታዊ የትዳር አጋር

ለዓለማት እዝነት የተላኩት ነብይ ለትዳር አጋራቸው ተገቢውን ውዴታ፤ ክብርና እንክብካቤ የሚለግሱ ተምሳሌታዊ የትዳር አጋር ነበሩ። እጅግ የሚወዷት ባለቤታቸው የሙዕሚኖች እናት ዓኢሻ እንዲህ ስትል ምስክርነት ሰጥታለች፦ **"የአላህ መልዕክተኛ በቤት ውስጥ የትዳር አጋራቸውን (በስራ) ያግዙ ነበር። ልብሳቸውን ይሰፉና ጫማቸውን ይጠግኑ ነበር። እንደማንኛውም ሰው የቤት ውስጥ ስራዎችን ያከናዉኑ ነበር።"** (አህመድ 25341)

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "(ሴቶችን) በመልካምም ተኗኗሩዋቸው።"
>
> ቁርኣን 4:19

ይህ የነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) መልካምነት ቤተሰባቸው ላይ ብቻ የተገደበ አልነበረም። ይልቁንም ሙስሊሞች ሁሉ የእርሳቸውን ፈለግ እንዲከተሉና ለትዳር አጋራቸው መልካም የህይወት ጓደኛ እንዲሆኑ እንዲህ ሲሉ ምክር ሰጥተዋል፦ **"የተሟላ እምነት ያለው እማኝ ማለት የተሻለ ሰነ ምግባር ያለውና ለትዳር አጋሩ በተሻለ ጥሩ የሆነው ነው።"** (አህመድ 24204)

CONTENTS






# መልካም አርአያ

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ!"
>
> ቁርኣን 68:4

በጥቂቱ የነብዩ ሙሐመድን ማንነት ለመጥቀስ ተሞክሯል። ስለ ኢስላምና ስለዚህ ታላቅ ሰብዕና አንዳንድ መገናኛ ብዙሀን የሚነዙትን መሠረተ-ቢስ አሉባልታዎች መሰረት በማድረግ አይታቸውን ለገነቡ ሰዎች እነዚህ በእዝነት የተሞሉ እውነታዎች እንግዳ ሊሆኑባው ይችላሉ።

ኢስላምን ለመረዳት ካሰብን የኢስላም መሠረታዊ ምንጮች የሆኑትን ቁርኣንንና የመልክተኛውን አስተምህሮ መሰረት ማድረግ ግድ ይለናል። ከአንዳንድ ሙስሊሞች የተዛነፉ ተግባራት በመነሳት ኢስላም ላይ አሉታዊ አቋም መያዝ ከፍትሀዊነት የራቀ ይሆናል።

## ሙስሊም ያልሆኑ ታዋቂ ሰዎች ስለነብያችን ምን አሉ?

የህንድ ነጻነት እንቅስቃሴ የፖለቲካ መሪ ማህተመ ጋንዲ እንዲህ ብሏል፦
**"መልዕክተኛው እራሱን አለማካበዱ፣ ለገባው ቃል እውነተኛነቱ፣ ለጓደኞቹና ለምዕመናን ታማኝነቱ፣ በአምላኩና በያዘው ተልዕኮ ያሳየው ሙሉ መተማመን እና መሰል ባህሪያቱ እንጂ ችግሮችን ለመወጣት የበቃው በሰይፍ አልነበረም!"**

ታዋቂው እንግሊዛዊ ደራሲ ጆርጅ በረናርድ ሾው ስለሳቸው እንዲህ ብሏል፦
**“ዛሬ ላይ ዓለም ችግሮቹን የሚፈታለት እንደ ሙሐመድ አይነት ሰብዕና በእጅጉ ያስፈልገዋል። በመሐከለኛው ዘመን የኖሩ የሀይማኖት አባቶች በዕውቀት ማነስ ወይም በጭፍን ጥላቻቸው ምክንያት ስለ ሙሐመድ ሃይማኖት የተዛባ ጨለምተኛ ምስል ለማስቀመጥ ሞክረዋል። የኢየሱስ መንገድ ጠላት አድርገው ስለውታል። በግሌ ስለዚህ ሰው ማንነት ባደረግኩት ጥናት የድንቅ ተዐምራዊ ሰብዕና ባለቤት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በጭራሽ የኢየሱስ መንገድ ጠላት እንዳልሆነ ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ። እንዲያውም የሠው ልጆች መድህን ተብሎ ሊሠየም ይገባዋል። በግል እስተያየቴ ዛሬ የዓለም ጉዳዮችን ሙሐመድ ቢመራቸው የሰው ልጆች የሚናፍቁትን ሠላምና ደስታ በማረጋገጥ ችግሮቻቸውን እንደሚቀርፍ አምናለሁ። የአውሮፓን ግዛት እንደ ሙሐመድ አይነት ሰው ቢመራው ከህመሞቹ ሁሉ እንደሚፈውሰው አምናለው። አዎን! ሙሐመድ የሰው ልጆች መድህን ተብሎ ሊጠራ ይገባል!”**

CONTENTS


ስለ ኢስላም አጭር ትውውቅ

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን)

መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው

የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም

ቁርኣን ለመላው የሰው ዘር የመጨረሻው ራዕይ

የህይወት አላማ ምንድን ነው?

ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች

የሴቶች መብቶች በኢስላም

የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር

ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም


# መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው

AMHARIC | (03/10) النبي عيسى عليه الصلاة والسلام | FREE COPY

ሙስሊሞች ሁሉ እየሱስን (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ይወዳሉ።

የእምነትህን መሰረቶች ተማር


جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES

Your Path To Peace..


مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
التعريف بالإسلام

تصريح رقم:
(2017/139)

دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

www.islamicic.com

CONTENTS


























ኢየሱስ በአለም ላይ ሚሊዮኖች የሚወዳቸው ሰብዕና ናቸው። ሆኖም እኚህን ታላቅ ሰብዕና ከመውደድና ክብር ከመቸር ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ በርካታ የተዛነፉ አመለካከቶችና ግድፈቶች አሉ። ሙስሊሞችም ክርስቲያኖችም ለዒሳ (ኢየሱስ) (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከፍተኛ ቦታና ክብር ይሰጣሉ። ኢየሱስን ይወዷቸዋል። በዚህ አይለያዩም! ነገር ግን እውነተኛ ማንነታቸውን አስመልክቶ እንደ ሰማይና ምድር የተራራቁ እይታዎችና አቋራረጦች አሏቸው።

ይህ በራሪ ጽሑፍ ከዒሳ (ኢየሱስ) (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ግልጽ ለማድረግ ያለመ ነው። ክርስቶስ አምላክ ነበሩን? ወይስ ከአላህ የተላኩ መልእክተኛ ነበሩ? መሲሑ ዒሳ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ማን ናቸው?

# ኢየሱስ እንደ አምላክ

ብዙ ክርስቲያኖች ኢየሱስ አምላክ ወይም የሰላሴ አንዱ አካል እንደሆኑ ይሞግታሉ። ይህም አምላክ በምድር ላይ በኢየሱስ መልክና ቅርፅ እንደተገለፀ ይናገራሉ። እንደ እነርሱ አባባል አምላክ በሰው ልጆች ቅርጽና አካል ተገልጧል። ሆኖም በእጃቸው የሚገኘውን መጽሀፍ ቅዱስ መሠረት በማድረግ እውነታውን ስንመረምር፤ ዒሳ መወለዳቸውን ፣ እንደማንኛውም ሰው መብላት መጠጣታቸውን፣ ብሎም ወደ አምላካቸው ፀሎት ማድረጋቸውንና የተገደበ እውቀትም እንደነበራቸው እንረዳለን። እነዚህ ፈጽሞ የፈጣሪ አምላክ መገለጫዎች ሊሆኑ እርሱንም ሊገልፁ አይችሉም! አምላክ ልዕልናው ከፍ ያለና በመልካም ባህሪያት የሚገለጽ ከጉድለትም የፀዳ ሲሆን የሰው ልጅ ግን ፍጡር እንደመሆኑ ጉድለት አያጣውም። ታዲያ እነዚህ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች በተመሳሳይ ግዜ እንዴት አንድ ላይ ሊገኙ ይችላሉ?

ኢስላም እንደሚያስተምረን አምላክ ሁልግዜም የተሟላ መገለጫዎች አሉት። አምላክ ሰው ሆነ የሚለው እምነት፤ ለተወሰነ የግዜ ምዕራፍ አምላክ ምሉዕነቱን አጥቶ በጉድለትም ተገልጾ ነበር እንደ ማለት ነው። ፈጣሪ አምላክ ከዚህ ፍፁም የጠራና የላቀ ነው።

አንድ ክርስቲያን ሰው እራሱን መጠየቅ የሚገባው ነገር አለ። በአንድ ወቅት ደካማና አቅመ ቢስ ሕፃን በነበረ፣ ወይም ያለ ምግብ፣ መጠጥና እንቅልፍ መኖር የማይችል “ሰው" በነበረ አምላክ ያምናልን? ከዚያም ይሄ ራሱ በብሉይ ኪዳን የተገለጸው ታላቅ አምላክ ይሆናልን? "በፍፁም!"

**“አምላክ ሁሉን ማድረግ የሚችል ከሆነ ለምንድን ነው ሰው መሆን የማይችለው?” ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል።**

እንደ ትርጓሜ አምላክ የፍጡራንን ደካማ ተግባራት የሚያንፀባርቅ አይደለም። ፍጡራንን በድርጊቶቻቸውም ሆነ በመገለጫዎቻቸው አይመስላቸውም። ከእርሱ የሚንፀባረቀው ፍጹምነት ብቻ ሲሆን፣ የሚገለጸውም በልቅና መገለጫዎች ብቻ ነው። ስለዚህ፣ አምላክ ከፍጡራኑ አንዱ ቢሆን፣ ወይም የእነርሱን መገለጫዎች ቢላበስ ኖሮ፣ በግድ አምላክ መሆኑ ያበቃ ነበር ማለት ነው።

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ጥቅል መልዕክት ያላቸው አንቀጾች በተሳሳተ መልኩ "ኢየሱስ አምላክ ነው" ለሚለው እምነት ደጋፊ ተደርገው ሊቀርቡ ይችላሉ። ይህ አካሄድ ግን ፈጽሞ ስህተት ነው። አዎን! የመጽሀፍ ቅዱስ አንቀጾችን በአንክሮ ስንመረምር በተደጋጋሚ የምናገኘው እውነታ ዒሳ ኢየሱስ የአላህ መልዕክተኛ የሆኑ ሰው መሆናቸውን ብቻ ነው። ከዚህ ያለፈ እውነታ አናገኝም!

እንደውም መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ ከፈጣሪ ሙሉ በሙሉ የተለዩ መሆናቸውን በግልጽ የሚጠቁሙ ንግግሮችንና ተግባሮቻቸውን እናገኛለን። ለምሳሌ፦

- በማቲዎስ ወንጌል (26:39) ላይ **“ኢየሱስ በግንባሩ ተደፍቶ በመስገድ እንደፀለየ" ተገልጿል። ኢየሱስ አምላክ ከሆኑ፤ በግንባራቸው ተደፍተው መፀለያቸውን ንጹህ አይምሮ ይቀበለዋልን? ለማን ነበር ይህ “አምላክስ” የሚሰግደው?**
- ክርስቶስ (መሲህ) በክርስትያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢይ ተብሎ ተገልጿል (ማቴዎስ 21:10-11)። **ታዲያ ክርስቶስ በተመሳሳይ ጊዜ እንዴት አምላክም ከአምላክ የተላከ መልእክተኛም ሊሆን ይችላል?!**

CONTENTS






- ኢየሱስ እንዲህ ማለታቸውንም መጽሀፍ ቅዱስ ይነግረናል፤ "**የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ እብ ይበልጣልና ወደ እብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር።**" (ዮሐንስ 14:28)
- ክርስቶስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ እርጋለሁ።" (ዮሐንስ 20:17)
- ክርስቶስ አምላክ ከሆኑ፣ "አባቴና አባታችሁ፣ አምላኬና አምላካችሁ" የሚለው ለምንድን ነው? ወደ ማንስ ነው የሚያርገው?

ኢየሱስ አምላክ ቢሆኑ ኖሮ ሰዎችን ግልጽ በሆነ ቋንቋ እንዲያመልኳቸው ይነግሯቸው ነበር። "አዎ" ብዙ የመጽሀፍ ቀዱስ አንቀጾችም ይህንን እውነታ ፍንትው አድርገው ባሣዩም ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ማንንም ያመልካቸው ዘንድ አላዘዙም። ማንንም ቢሆን ፈጣሪ አምላክ አድርጎ እንዲገልፃቸው አልፈቀዱም። እንዲያውም "የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል" በማለት እርምት ሰጥተዋል። (ማቲዎስ 15:9)

# “የአምላክ ልጅ”

አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ክርስቶስ የአላህ ልጅ ነው ብለው ይሞግታሉ። ይህ ምን ማለት ነው? አላህ ልጅ ከመውለድ እጅግ የላቀ ነው። ሰዎች ሰዎችን ይወልዳሉ። ሁሉም ፍጡራንም እንደዚሁ ናቸው። ታዲያ ለአምላክ ልጅ መውለድ ምን ማለት ነው?!

የመጽሀፍ ቅዱስን አገላለጽ ስናጤን፤ በቀጥተኛ ትርጓሜ ፈንታ "የአምላክ ልጅ" ለሚለው ገለጻ ዘይቤያዊ ትርጓሜ ሲሰጥ እናያለን። ይህም "ፃድቅ የአምላክ ባሪያ" ለማለት ሲሆን በዚሁ መጽሀፍ ውስጥ ይህንን ገለጻ ለኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ለዳዊት ለሠለሞን እና ለያዕቆብ ሲውል እናያለን። በመፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል እናገኛለን፦ "እስራኤል (ያዕቆብ) የበኩር ልጄ ነው።" (ዘፀዓት 4:22)

በእርግጥም "ልጅ" የሚለው ቃል ከአላህ ወንድ ባሪያዎች ጻድቅ ወንዶችን ሁሉ እንዲሁም ከአላህ ሴት ባሪያዎች የሆኑ ጻድቅ ሴቶችን ሁሉ ያመለክት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዲህ ይላልና፦ "በጌታ መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የጌታ ልጆች ናቸው።" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8:14)።

ሆኖም በዚህኛው ዘይቤያዊ ትርጓሜም ቢሆን የአምላክ ልጅ በሚል መግለጽ በራሱ ለተሳሳተ ግንዛቤ ሊያበቃ ይችላልና ተቀባይነት የለውም።

> በክቡር ቁርኣን ይህንን አጠቃቀም የሚያወግዙ በርካታ አንቀጾችን እናገኛለን። “ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም። (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ። ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው ‘ሁን’ ነው፤ ወዲያውም ይሆናል።”
>
> ቁርኣን 19:35


# "አባትና አምላክ"

በተመሳሳይ መልኩ፣ "እብ" (አባት) የሚለው ቃል ሲጠቀስ ጥሬ ቃሉን በቀጥታ መውሰድ አይገባም። ምክንያቱም አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪና ሲሳይ ሰጪ መሆኑን ለማመልከት ያገለግል ነበርና። "እብ" የሚለው ቃል በዘይቤያዊ መንገድ ጥቅም ላይ እንደዋለ የሚያረጋግጡ ብዙ ጥቅሶች አሉ። ለዚህ ምሳሌ ከሚሆኑ አንቀጾች መካከል ይህንን እናገኛለን፦ "አንድ አምላክና የሁሉ አባት።" (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:6)

ሆኖም ከላይ እንደተጠቆመው በትክክለኛ ትርጓሜም ቢሆን ልጅነትን እና አባትነትን ከአምላክ ጋር አቆራኝቶ ጥቅል በሆኑ መልኩ መግለጽ ጉድለትን የሚያመለክት መልዕክት ስለሚያስተላልፍ የተፈለገበት ትርጓሜ ምንም ቢሆን በቅዱስ ቁርኣን በተደጋጋሚ ተወግዟል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት "ጌታ" ብለው ይጠሯቸው ነበር። ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ እነጋገሮች ውስጥ አምላክን ለመግለጽ እንዲሁም ከፍተኛ ቦታ ያላቸውን ሰዎች ለማመልከት ያገለግል ነበር። ለምሳሌ፣ በግሪክ አዲስ ኪዳን ውስጥ "kyrios" የሚለው ቃል "ጌታ" የሚለውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል። እንዲሁም ክቡር ሰው (ማቴዎስ 20:8) እና አመፀኛ አገልጋዩን የሚመታ ጌታ ለመግለጽም ይውላል። (ሉቃስ 20:42-47)

CONTENTS





























በሌሎች የወንጌል ክፍሎች ደግሞ ኢየሱስን (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ደቀመዛሙርቱ ፦ "የአምላክ አገልጋይ" በማለት ይጠሯቸዋል። “የአባቶቻችን አምላክ፥ አገልጋዩን ኢየሱስን አከበረው።” (የሐዋርያት ሥራ 3:13)

ይህም "ጌታ" የሚለው ቃል ከዒሳ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ጋር ሲያያዝ ለክብር እንጂ ለአምላክነት አይደለም የሚለውን በግልጽ ያሳያል።

# ነብዩ ኢየሱስ

አይሁዶች በወቅቱ ሲጠበቅ የነበረው የአምላክ መልዕክተኛ አልመሲህ ዒሳ መሆናቸውን አስተባብለዋል። ይህ ደግሞ ክርስቶስ አምላክ ተደርገው ወይም የአምላክ ልጅ ተደርገው ከሚመለኩበት የክርስትና ትምህርት ጋር ሙሉ በሙሉ ይቃረናል።

ኢስላም ግን በእነዚህ ሁለቱ መሀል መካከለኛ መንገድ ነው። የመርየም ልጅ ዒሳ ከአላህ የተላኩ የተከበሩ መልዕክተኛ መሆናቸውን እንዲሁም ሲጠበቅ የነበረው መሲህ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ሆኖም ግን፣ እሰልምና ከደረጀቸው በላይ ከፍ አላደረጋቸውም፤ አምላክም አላደረጋቸውም። ምክንያቱም አምልኮ የሚገባው ዒሳንና ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረው አንድ አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) ብቻ ነውና።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “(ዒሳ) አለ፡ ‘እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ። መጽሐፍን ሰጥቶኛል፣ ነቢይም አድርጎኛል።’”
>
> ቁርኣን 19:30

# ተአምራዊው ውልደት

በተከበረው ቁርኣን መሰረት፣ ጂብሪልን (ገብርኤል) (ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን) አላህ በሰው አምሳል ወደ ንጽሕቷ መርየም (ማርያም) ልኮቷል። እርሱም ያለ ወንድ ንክኪ፣ በመለኮታዊ ተአምር ወንድ ልጅ እንደምትወልድ አበሰራት።

**የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ " ‘እኔ ንጹሕን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ’ አላት። ‘(በጋብቻ) ሰው ያልነካኝ ሆኜ አመንዝራም ሳልሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል?!’ አለች። ‘(ነገሩ) እንደዚህ ነው፤ ጌታሽ፡ ‘እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው፤ ለሰዎችም ታምር ከእኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሠራን) የተፈረደም ነገር ነው’ ብሏል’ አለ። (ነፋባትም።)"**

ቁርኣን 19:19-21

አንዳንዶች ግን ይህ ተዓምራዊ ውልደታቸው አምላክነታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ነው ብለው ይሞግታሉ። ይሁን እንጂ፣ ክርስቶስ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ያለ አባት ወደዚህ ዓለም የመጡ የመጀመሪያው ሰው አይደሉም። ከርሳቸው በፊት አደም (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ነበሩ። እርሳቸው አባትም ሆነ እናት አልነበራቸውም። አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) እንዲህ ብሏል፦

**"አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አደም ብጤ ነው። ከዐፈር ፈጠረው። ከዚያም ለርሱ (ሰው) ‘ሁን’ አለው፤ ሆነም። ይህ ከጌታህ ዘንድ የሆነ እውነት ነው። ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን።"**

ቁርኣን 3:59-60

እየሱስ ያለ አባት በመወለዳቸው የሚመለኩ ከሆነ፣ አዳም ከሳቸው በበለጠ አምልኮ የሚገባቸው ይሆናሉ። ምክንያቱም ያለ አባትና ያለ እናት የተፈጠሩ ናቸውና።

CONTENTS






# የኢየሱስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ተዓምራት

የኢየሱስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ተዓምራት ያለ አባት በመወለዳቸው ላይ የተገደቡ አልነበሩም። አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) በፈቃዱ በርሳቸው እጅ ብዙ አስደናቂ ተዓምራትን አሳይቷል።

በዝሙት ከተወነጀለች እናታቸው ለመከላከል ገና በእቅፍ ውስጥ ያሉ ጨቅላ ህጻን ሆነው ሳለ ሰዎችን አናግረዋል። እንዲሁም የተከበረው ቁርኣን እየሱስ ሙታንን በአላህ ፈቃድ ሕያው ሲያደርጉ እንደነበር፣ እንዲሁም ለምጻሞችንና ዕውሮችን በአላህ ፈቃድ ሲፈውሱ እንደነበር ጠቅሷል።

እነዚህ ሁሉ ተዓምራት በእርሳቸው እጅ መፈጸማቸው፣ የአላህ አገልጋይና መልክተኛ፣ ለፈጣሪ ታዛዥ እንደነበሩ ከማመላከታቸው ውጭ ሌላ ምንም ትርጉም የላቸውም። እንደ እውነታው ከሆነ፤ ብዙ ተዓምራት በብዙ የአምላክ መልእክተኛ ነብዮች እጅ ተፈፅመዋል። ለምሣሌ ኑህ ፣ ሙሳ ፣ ሙሐመድን መጥቀስ እንችላለን፤ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሁሉም ላይ ይሁን)። በእነርሱ እጅ የተፈጸሙት ተአምራት በሙሉ በአላህ ትዕዛዝና ፈቃድ ብቻ የተፈፀሙ ሲሆኑ እውነተኝነታቸውን በማረጋገጥ ጥሪያቸውን ለማጠናከርና ለማስረጽ ተገልግለውበታል።

# የኢየሱስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ተልዕኮ

አብርሃም፣ ኖኅ እና ዮናስን የመሰሉ የብሉይ ኪዳን ነቢያት አምላክ የሰላሴ አካል ነው ብለው በፍጹም አላስተማሩም። ኢየሱስንም አዳኛቸው አድርገው አላመኑም።

የነሱ ጥሪ ከሰሩ ምንም ደመና እንደሌለበት እንደ ቀትር ፀሐይ ፍንትው ያለ ነበር። እርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ የለም፤ ከአንድ እርሱ ውጪ ማንም ለአምልኮ አይገባም የሚል ነው።

አላህ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት በሺዎች የሚቆጠሩ መልእክተኞችን በተመሳሳይ እምነትና መልእክት እየላከ ከቆየ በኋላ፣ በድንገት ቀይሮ እርሱ ከሶስቱ ሰላሴዎች አንዱ እንደሆነ ወይም ክርስቶስ ልጁ እንደሆነ እና “የመዳኛው እምነት ይህ እምነት ብቻ ነው!” ማለቱ ከአእምሮም ከምክንያትም የራቀ ነው።

ፍንትው ያለው እውነታ ግን ምንም የተቀየረ መልዕክት አለመኖሩ ሲሆን ኢየሱስም የተጣሩት የቀድሞ ዘመን ነብያት ወዳስተማሩት ጥሪ ብቻ ነው። ምንም የቀየሩትና የለወጡት ነገር የለም። ይህ ነብያዊ ጥሪ፣ እምነትና ተግሳጽ በኢየሱስም ዘመን ነበር። የዚህን መልእክት ዋና ይዘት የሚያረጋግጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነትም አለ። ይህም እንዲህ የሚለው የእየሱስ ንግግር ነው፦ “ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ እስራኤል ሆይ፣ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።” (ማርቆስ 12:28)

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “ዒሳ በታምራቶች በመጣ ጊዜም አላቸው: ‘በእርግጥ በጥበብ መጣኋችሁ። የዚያንም በርሱ የምትለያዩበትን ከፊሉን ለናንተ ላብራራላችሁ (መጣሁ)። አላህንም ፍሩ። ታዘዙኝም። አላህ ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።’”
>
> ቁርኣን 43:63-64

ስለዚህ እንደ እየሱስ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አስተምህሮ፣ ከምንም ነገር በላይ ታላቁ ትእዛዝ እና መሰረታዊው እምነት "አምላክ አንድ ነው" የሚለው ነው።

እየሱስ አምላክ ቢሆኑ ኖሮ “እኔ አምላካችሁ ነኝና አምልኩኝ” ማለት ይችሉ ነበር። ነገር ግን ከዚህ ይልቅ የአላህን አንድነት የሚያረጋግጡ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ደግመው ደጋግመው ያስተጋቡ ነበር።

CONTENTS






ይሄ ጉዳይ የኢየሱስ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) መልእክት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚገጥም ነው። እንዲሁም የእስልምና ትምህርቶች ጋርም ይገጥማል። እስልምና ኢየሱስ ወደ እስራኤል ልጆች ከአላህ ዘንድ የተላኩ መልእክተኛ መሆናቸውን ይደመድማል። እርሳቸውም መልእክተኞች ወደ ሰው ልጆች በሙሉ የተላኩበትን ተመሳሳይ መልእክት ይዘው የመጡ ናቸው፡- ከአላህ ውጪ ለአምልኮ የሚገባ ሌላ አምላክ የለም።

እየሱስ ሙስሊም ነበሩ። እንዲሁም እንደማንኛውም መልዕክተኛና ባሪያ ለአላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) ትእዛዛት ታዛዥና የተገዙ ነበሩ። ሁኔታቸው እንደማንኛውም መሻቱን፣ ትኩረቱን፣ ንግግሩንና ተግባሩን ለአላህ እንዳደረገ ሙስሊም ናቸው።

# ኢየሱስ በኢስላም

ኢየሱስ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ከአላህ ነቢያት ውስጥ አንዱ ነበሩ። አላህም ሰዎችን ወደ አንድነቱ (ተውሒድ) እንዲጠሩ ልኳቸዋል።

ይህ ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽ ሲሆን፣ የተከበረው ቁርኣንም አረጋግጦታል። ኢየሱስን (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) የሚመለከተው ኢስላማዊው እምነት ኢየሱስ እንዴት ተአምራት በእጃቸው የሚፈጸሙላቸው መልእክተኛ እንደነበሩ ያብራራል። በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ፣ የአላህን አንድነትና ፍጹምነት ይጠብቃል።

አንባቢ ሆይ! እኛ እስልምናን በተመለከተ የበለጠ እንድትመረምርና እንድትጣራ እንጋብዝሃለን። እርሱ (እስልምና) ሌላ ሃይማኖት አይደለም። ይልቁንም ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ዒሳ እና ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሁሉም ላይ ይሁን) የተላኩበት መልእክት ነው። እስልምና ማለት "ለአላህ መገዛት" ማለት ሲሆን የሰው ልጅ፣ ከአላህ ጋር ባለው ግንኙነት እንዲሁም ከፍጡራኑ ጋር ባለው ግንኙነት መልካም እንዲሰራ የሚያበረታታ የተሟላ የህይወት መንገድ ነው።

እስልምና አላህ ፍትሐዊና መሐሪ እንደሆነ ያስተምረናል። ኃጢአቶችን ለመማርና መከራዎችን ለመመለስ ራሱን ወይም ልጁን መስዋዕት ማድረግ አያስፈልገውም። እንዲሁም አንድ ሰው ያልፈፀመውን ብናኝ የምታህል ወንጀል እንኳ አይጽፍበትም። አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) እያንዳንዱን ሰው በራሱ ሥራ ነው የሚጠይቀው። እያንዳንዱ ሰው ለሰራው ነገር ተጠያቂ ነው።

እስልምና ሁሉንም የአላህ ነቢያትን መውደድንና ማክበርን ያስተምረናል። ነገር ግን፣ ለእነርሱ ያለን ውዴታና አክብሮት እነርሱን እናመልካቸዋለን ማለት አይደለም። አምልኮ የሚገባው ለአላህ ብቻ ነውና። ኢየሱስን ከአላህ ዘንድ የተላኩ መልእክተኛ እንደሆኑ ማመን እና እስልምናን መቀበል፣ ከኢየሱስ መልእክት መውጣት ማለት አይደለም። ይልቁንም የእርሳቸው (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁንና) መሰረታዊ መልእክታቸውና የመጀመሪያ ጥሪያቸው ነው።


HOTLINE
+971 56 204 2045
islamicicdxb
islamicic.com info@islamicic.com +971 4 355 5223
DOWNLOAD AMHARIC FLYERS
www.iicdxb.com/amharic

CONTENTS

ስለ ኢስላም አጭር ትውውቅ
ነብዩ ሙሐመድ
መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው
የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም
ቁርኣን
የህይወት አላማ ምንድን ነው?
ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች
የሴቶች መብቶች በኢስላም
የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር
ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም

# የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም

AMHARIC (04/10) مفهوم الإله في الإسلام FREE COPY

## ከፈጣሪ (ጥራትና ልቅና ይገባው) የሚበልጥ ማንም የለም።

Dar Al Ber Society
www.daralber.ae
الإمارات
THE EMIRATES
Your Path To Peace..
مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام
www.islamicic.com
دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department
تصريح رقم:
(2017/139)

CONTENTS



# እውነት አምላክ አለ?

ለዚህ ዓለም አምላክ መኖሩን የሚያረጋግጡ በርካታ አእምሯዊ ማስረጃዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ሦስቱን ቀጥሎ እንዘረዝራለን፦

## 1. የዩኒቨርሱ ስርዓት

ስፊ የባሕር ዳርቻ ላይ እየተጓዝክ ሳለህ አንድ ሰዓት በአሸዋ ውስጥ ብታገኝ፣ ያ ሰዓት በአሸዋው ውስጥ በአጋጣሚ እንደተፈጠረና እንደተገኘ በፍጹም አታስብም። የሰዓቱ ውስብስብና የተሳሰሩ አጠቃላይ ክፍሎች በአሸዋ ውስጥ ከነበሩ ቁሳቁሶች በአጋጣሚ እንደተፈጠሩ በፍጹም አታምንም። ይህ ሰዓት የራሱ ሰሪና ፈጣሪ ሊኖረው ይገባል። ይህ ሰዓት ትክክለኛውን ጊዜ በሚል ይተካ የመናገር ዓላማ ካለው፣ ሰሪው አዋቂ መሆን አለበት። ተፈጥሮአዊ አጋጣሚ ደግሞ ትክክለኛና ቁርጥ ያለ ሥርዓት ያለው ሰዓት ፈጽሞ ማምጣት አይችልም ።

ምድርን ስንመለከት፣ በፀሐይ ዙሪያ የምትሽከረከርበት ሥርዓት እጅግ በጣም ትክክለኛ በሆነ ጊዜ የተደራጀና የተስተካከለ ነው። ይህም ሳይንቲስቶች የፀሐይ መውጣትና መጥለቂያ ጊዜዎችን አስቀድመው እንዲወስኑ አስችሏቸዋል። ሰዓት ትክክለኛ ጊዜውን የሚወስን አዋቂ ሰሪ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ ምድርም በፀሐይ ዙሪያ የምትሽከረከርበትን ጊዜ በትክክል የወሰነ አዋቂ ሰሪ ሊኖራት ይገባል። ይህ በራሱ ሊሆን ይችላልን?!

በተመሳሳይ መልኩ፣ በራሳችን ውስጥና በአጠቃላይ በዓለም አድማስ ውስጥ ረቂቅ ስርዓቶችንና ሕጎችን ስንመለከት፤ ይህ ዓለም አደራጅ ሊኖረው አይገባምን? እና ለዚህ "አደራጅ" ምርጡ ማብራሪያ ይህንን ዓለም የፈጠረና ያደራጀ አንድ ቻይ አምላክ መኖር ነው።

## 2. የፍጥረተ ዓለም (univers) አፈጣጠር

ዘመናዊው ሳይንስ ይህ ዓለም መጀመሪያ እንዳለው ይደመድማል። ይህም ዓለም እየሰፋ መሄዱን በቅርብ ጊዜ በተደረገው ግኝት ላይ የተመሠረተ ነው። ጊዜን ወደኋላ ብንመልስ፣ ዓለም ወደጀመረበት ነጥብ ይመለሳል። የዓለም አፈጣጠር ሦስት ሊሆኑ የሚችሉ ማብራሪያዎች አሉ። እነሱም፦

1. ዓለም ከምንም ነገር ተፈጠረ።
2. ዓለም ራሱን ፈጠረ።
3. ዓለም የተፈጠረ ነው።


ለሁለተኛው ማብራሪያ፣ ቀላል አመክንዮ የሚነግረን አንድ ነገር ከመኖሩ በፊት ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችል ነው። ይህ ደግሞ፣ የዓለም አመጣጥ ብቸኛው ምክንያታዊ ማብራሪያ ሦስተኛው እንደሆነ ያሳያል። ይኸውም ፈጣሪ፣ ቻይ፣ ጥበበኛና ሁሉን አዋቂ የሆነ አምላክ እንደፈጠረውና እንዳደራጀው ነው።

> የሰው ልጅ ተሞክሮ እንደሚያሳየን መጀመሪያ ያላቸው ነገሮች ከምንም ነገር ሊገኙ አይችሉም።

አንዳንድ ሰዎች "አላህን ማን ፈጠረው?" ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ።

ፈጣሪ አምላክ ከፍጡራኑ የተለየ ነው። እርሱ እንደ ፍጡራኑ ቢሆን ኖሮ፣ እርሱም ፈጣሪ አምላክ ያስፈልገው ነበር። ይህ ደግሞ ማለቂያ የሌላቸው ፈጣሪ አማልክት እንዲኖሩ ያደርጋል። ይህ የማይቻል ነገር ነው። ፈጣሪ አምላክ ከዚህ ዓለም የጊዜና የቦታ ወሰኖች በላይ ነው። እርሱ ዘላለማዊ

CONTENTS

























ህልውና ያለው፣ መነሻ የሌለው የመጀመሪያ፣ ፍፃሜ የሌለው የመጨረሻ ነው። ስለዚህ፣ ለፈጣሪ ፈጣሪ አለው ወይ ብሎ መጠየቅ ምክንያታዊ ያልሆነና አመክንዮ የጎደለው ጥያቄ ነው።

## 3. ከአላህ የወረደው ራዕይ

የእስልምና ቅዱስ መጽሐፍ ቁርኣን የአላህ ቃል መሆኑን የሚያሳዩ ግልጽ ጠቋሚ ምልክቶች አሉ። ይህንን የሚደግፉ ምክንያቶች አጭር ማጠቃለያ ከዚህ በታች ቀርቧል።

አላህ ለሰዎች የመመሪያ መጽሐፍን ካወረደ፣ ያ መጽሐፍ የአላህን መኖር የሚያሳዩ ግልጽ ማስረጃዎችን መያዝ አለበት።

ቁርኣን ከ1400 ዓመታት በፊት የወረደ ቢሆንም፣ በዚያን ዘመን ለሰዎች ይታወቁ ያልነበሩ፣ በቅርብ ጊዜ በዘመናዊ ሳይንስ የተገኙ በርካታ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ይዟል። ለዚህ ምሳሌዎች የሚሆኑት የሚከተሉት ናቸው፦ ውሃ የሁሉም ሕይወት ያላቸው ነገሮች መነሻ መሆኑ (አል-አንቢያእ፡ 30)፣ የዩኒቨርስ መስፋፋት (አዝ-ዛሪያት፡ 47)፣ እንዲሁም የፀሐይና የጨረቃ እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆኑ ምህዋሮች መኖራቸው (አል-አንቢያእ፡ 33)።

ቁርኣን በዚያን ጊዜ ለሰዎች ይታወቁ ያልነበሩ በርካታ ታሪካዊ እውነታዎችን የያዘ ሲሆን፣ ትንቢቶችም በኋለኛ ጊዜ እውነት ሆነው መገኘታቸው ተረጋግጧል።

ቁርኣን ከየትኛውም ስህተቶች ወይም ተቃርኖዎች የጸዳ ነው።


- ቁርኣን ከሌሎች መጽሐፎች በተለየ መልኩ በመጀመሪያው ቋንቋው በዐረብኛ ከወረደበት ጊዜ ጀምሮ ቃል በቃል ተጠብቆ ቆይቷል። ሌሎች መጽሐፎች በመጀመሪያ ቅርጻቸው የሉም።
- ቁርኣን ግልጽ፣ ንጹህና ዓለም አቀፋዊ መልእክት የያዘ በመሆኑ ስለ አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) ያሉትን ጥልቅ አስተሳሰቦችና እምነቶች የሚዳስስ ነው።
- ቁርኣን የተወረደው መፃፍና ማንበብ የማይችሉ በነበሩት ነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ነው። ሆኖም፣ ልዩ የሆነ የቋንቋ ዘይቤን የያዘ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዐረብኛ የአነጋገር ምጥቀትና የቋንቋ ውበት ቁንጮ እንደሆነ ይታወቃል።

ቁርኣን ብዙ ልዩና ተዓምራዊ ገጽታዎች በጣም ምክንያታዊ ማብራሪያ መያዙ ከአላህ ዘንድ የወረደ በመሆኑ ነው።

# እምላክ ማነው?

"አላህ" የአንድና የእውነተኛው አምላክ የተለየ ስም ነው። በዚህ ስም ሌላ ምንም ነገር ሊጠራ አይቻልም። ይህ ቃል በብዙ ቁጥር ወይም በአንስታይ አይገኝም። ከእንግሊዝኛው ቃል "God" በተለየ ማለት ነው። ይህኛው በብዙ ቁጥር ("gods") ወይም በሴት ጾታ ("goddess") ሊገለፅ ይችላል። "አላህ" የሚለው ቃል በኢስላም ውስጥ ያለው ልዩ አጠቃቀም፣ ኢስላም በአላህ ፍጹም አንድነት መርህ ላይ ምን ያህል አፅንዖትና ትኩረት እንደሚሰጥ ያንፀባርቃል።

CONTENTS

































በእስልምና ውስጥ ካሉ ውብ ነገሮች ሁሉ፣ (ኢሰላም በሙሉ ውበት ቢሆንም)፣ የላቀው አላህን ፍጹምነት፣ ታላቅነትና አንድነት መገለጫዎች በሙሉ ማረጋገጥ ነው። ይህ ደግሞ አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) እና ስሞቹና መገለጫዎቹን በሚመለከቱ የእስልምና ትምህርቶች ውስጥ በግልፅ ይታያል።

> “እምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው። ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም።”
>
> ቁርኣን 2:163

## የላቀው አላህ አንድ ነው!

- የላቀው አላህ ተጋሪዎችም ብጤዎችም ሆነ ተቀናቃኞች የሉትም።
- የላቀው አላህ አባትም ሆነ እናት የሉትም። ወንድም ይሁን ሴት ልጅን ወይም ሚስትን አልያዘም።
- የላቀው አላህ ብቻውን ለአምልኮ የተገባ ነው።
- ከአንድ በላይ አምላኮች ቢኖሩ ኖሮ፣ ይህ በኃይላቸውና በዓለም ላይ ባላቸው ችሎታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድር ነበር። ምክንያቱም በእርግጠኝነት ከሌሎች አማልክት ጋር ግጭት ወይም ፉክክር ይኖር ነበርና።

## የላቀው አላህ ሁሉን ቻይ ነው!

- አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) የሁሉም ነገሮች ቁልፎች በእጁ ናቸው። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው።
- የሁሉም ነገር እናቱ በአላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) እጅ ነው (በእርሱ ቁጥጥር ስር ነው።) ወደ ሲሳይ መምራትም በአላህ ላይ ነው።
- ለአላህ ታዛዥ የሆነ ሰው መታዘዝ አይጠቅመውም፣ ወንጀለኛ የሆነ ሰው መተላለፍም አይጎዳውም።

## የላቀው አላህ የበላይ ነው!

- አላህ ከርሱ በላይ ምንም ነገር የለም። የሚወዳደረውም የለም።
- የአላህ መገለጫዎች የፍጥረታቱን መገለጫዎች አይመስሉም።
- አላህ በማንኛውም ሰው ወይም በማንኛውም ነገር ውስጥ አይገለጽም።
- አላህ የፍጹምነት መገለጫዎች አሉት። በሌሎች ሃይማኖቶች ውስጥ ሰዎች እንደሚሉት የሰው ልጅ ድካም ውስንነቶች በእርሱ ላይ አይተገበሩም። ለምሳሌ ሰማያትንና ምድርን በሰድስት ቀናት ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን አረፈ እንደሚሉት።

## የላቀው አላህ ፍትሐዊ እና እዛኝ ነው!

- አምላክ ኃጢአቶችን ይቅር ለማለት ራሱን መሠዋት አያስፈልገውም። ምክንያቱም የትኛውም አካል ያልፈፀመውን ኃጢአት ተሸክሞ አይወለድምና።
- አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) እያንዳንዱን ሰው በሰራው ሥራ ብቻ ነው የሚመረምረው። ሁሉም ሰው በፈፀመው ተያዥ ነው።
- ሰዎች የአላህን (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) ውዴታ የሚያገኙት በእርሱ በማመንና መልካም ሥራ በመሰራት ነው። በዘር፣ በማኅበራዊ መደብ ወይም በሀብት አይደለም።

CONTENTS





## የዒሳ (ክርስቶስ) - ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን - ተፈጥሮ

አብዛኞቹ ክርስቲያኖች "ክርስቶስ አምላክ ነው" ወይም ከሦስቱ አንዱ ነው ብለው ያምናሉ። እንዲሁም እርሱ የአምላክ ምድራዊ መገለጫ ነው፣ እርሱም በሰው መልክ ያለ አምላክ ነው ብለው ያምናሉ።

> በእስልምና ውስጥ የአምላክን ጽንሰ-ሐሳብ ለማስረዳት ሲሞከር የዒሳን (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ተፈጥሮ መረዳት ወሳኝ ነገር ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በእርሳቸው ተፈጥሮ ዙሪያ ሰፊ የተሳሳቱ አመለካከቶችና ሙግቶች በመኖራቸው ነው።

ሆኖም ግን፣ በክርስትናው እምነት ቅዱስ መጽሐፍ መሠረት፣ ክርስቶስ የተወለደ፣ የሚበላ፣ የሚጠጣ፣ የሚተኛ፣ የሚጸልይ እና ጠቅላይና ሁሉገብ እውቀት ያልነበረው ነው። እነዚህ መገለጫዎች ደግሞ ለአምላክ አይገቡም። አምላክ የፍጹምነት መገለጫዎች ነው ያሉት። ሰው ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው። ታዲያ አንድ ነገር በአንድ ጊዜ በሁለት ተቃራኒ መገለጫዎች እንዴት ሊኖር ይችላል? ይህ ምክንያታዊ አይደለም።

ሆኖም፣ አንዳንዶች እንዲህ ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ፦ "አምላክ ሁሉን ቻይ ከሆነ፣ ለምን ሰው ሊሆን አይችልም?"

ከትርጓሜ ስንነሳ፣ አምላክ መለኮታዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን አያደርግም። ስለዚህ፣ አምላክ ሰው ሆኖ በሰውነት መገለጫዎች የሚገለፅ ከሆነ፣ የግድ አምላክ መሆኑ ያበቃል።

በተጨማሪም፣ በክርስትና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ክርስቶስ ራሱን የአላህ ባሪያ አድርጎ የሚናገርባቸውና የሚሠራባቸው፣ እንዲሁም አላህ ከእርሱ የተለየ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ ጥቅሶች አሉ።

ለምሳሌ፦ በዮሐንስ ወንጌል 8:40 ላይ እንዲህ ይላል፦ “ነገር ግን እኔ ከእምላክ የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁ ሰው ሰሆን፣ አሁን ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ።”

"አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ክርስቶስ የአምላክ ልጅ ነው ብለው ያምናሉ" የሚለውን አባባል ስንመለከት፣ እራሳችንን መጠየቅ ያለብን፣ ይህ በትክክል ምን ማለት ነው? የሚለውን ነው።


አላህ – በፍጹም እምነት – ቁሳዊ ልጅ ከመያዝ የላቀ ነው። ይልቁንም "የእምላክ ልጅ" የሚለው ቃል በቀድሞዎቹ ኦሪታዊ ቋንቋዎች ውስጥ "ጻድቅ አገልጋይ" የሚለውን ለመግለጽ በምሳሌያዊ አነጋገር እንደዋለ እናገኛለን። ይህ አገላለጽ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደ ዳዊት፣ ሰሎሞንና እስራኤል ላሉ ብዙ ጻድቃን ሰዎች በተደጋጋሚ ተጠቅሞበታል። ቃሉም ለክርስቶስ (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ብቻ የተወሰነ አይደለም።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ደግሞ "...እስራኤል የበኩር ልጄ ነው" ማለቱ ነው። (ኦሪት ዘጸአት 4:22)

> “ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም። (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ።”
>
> ቁርኣን 19:35

የእስልምና እምነት የዒሳን (ኢየሱስ) - ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን - እውነተኛ ማንነት በግልጽ ያሳያል። በተመሳሳይ ጊዜም ስለ አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) ስለ ታላቅነቱ፣ አንድነቱና ፍጹምነቱ ያለውን ትክክለኛ እምነት ይጠብቃል።

CONTENTS






















ዒሳ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) አላህ ወደ አንድ አምላክ ብቻ አምልኮ እንዲጠራ የላከው ክቡር መልእክተኛ ነበር።

## አላህ ብቻ ነው አምልኮ የሚገባው!

**"አላህንም ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ።" ቁርኣን 4:36**

የእስልምና አስተምህሮዎች የሚያተኩሩት ሁሉንም አምልኮታዊ ተግባሮቻችንን ለአላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) ብቻ መስጠት እንዳለብን ነው። ከእርሱ ውጭ ማንም አምልኮ የሚገባው የለም። ጣዖታት፣ መቃብሮች፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እንስሳት፣ ነቢያት፣ ጻድቃን ሰዎች፣ መላእክት፣ ሸይኾች ወይም ዑለማዎች ማንም የለም። እነዚህ ሁሉ ፍጡራንና ውስኖች ናቸው። ጉድለትና ድካም አለባቸው። አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) ግን ብቸኛ ፍጹም ነው።

## የላቀው አላህ በቀጥታ ያለ አገናኝና አማላጅ ይመለካል።

የላቀው አላህ ምንም ዓይነት ተጋሪዎች ወይም ወደሱ አገናኞች አያስፈልጉትም። በአላህና በሰው ልጆች ሁሉ መካከል ያለው መንገድ ክፍት ነው። እርሱ እንዳዘዘውና እንደወሰነው እርሱን ብቻ በቀጥታ ያመልኩታል። እርሱ የሚያመሰግነውን፣ የሚማፀነውን፣ የሚያመልከውንና ተስፋ የሚያደርገውን ሁሉ ይሰማል። አላህን በአገናኞችና በአማላጆች (እንደ ጣዖታት፣ ምስሎች እና ሌሎች አገናኞች) ማምለክ ግን የተውሒድን መሰረት ይንዳል። እንዲሁም አላህ ብቻውን ለአምልኮ ብቁ መሆኑን ይቃረናል።

## ሁሉም መልእክተኞች ወደ አላህ አምልኮ ጠርተዋል!

**"በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ 'አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ' በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።" ቁርኣን 16:36**

ሙስሊሞች የላቀው አላህ በላካቸው በሁሉም ነቢያት ያምናሉ፣ እንደ አደም፣ ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ዒሳ እና ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በነሱ ላይ ይሁን)። አላህ ሁሉንም የላካቸው በአንድ መልእክት ነው፦ "አላህን ብቻ አምልኩ፤ ከእርሱ ሌላ አምላክ የላችሁምና።"

## የህይወት ዓላማ... አላህን ማምለክ ነው።

የዚህ ሕይወት የመጨረሻው የህልውናችን ግብ አላህን ማምለክ፣ በአምላክነቱና ጌትነቱ ብቸኛ እንደሆነ ማመን፣ እርሱን ብቻ መገዛት፣ እና ውዴታውን መፈለግ ነው። በእስልምና የአምልኮ (ዒባዳህ) ጽንሰ-ሐሳብ እንደ ሶላትና ጾም ያሉ የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ ብቻ አይገደብም። ይልቁንም አላህ የሚወዳቸውንና የሚደሰትባቸውን ነገሮች በሙሉ ያጠቃልላል። ለምሳሌ የደጋጎችን መልካም ሥነ ምግባር፣ የታዛዦችን በጎ ተግባራት፣ የሠራተኞችን ትዕግሥት፣ እንዲሁም ለድሆችና ለችግረኞች መልካም መዋልን ፣ ... ይይዛል።

በመጨረሻም፣ የእስልምና መሠረት በአላህ (ጥራትና ልቅና ይገባው) አንድነትና ብቸኛነት ማመን ነው። እርሱ የፍጹምነት መገለጫዎች ያሉት የሁሉ ነገር ፈጣሪና ጌታ ነው። እናም እርሱ ብቻ ለአምልኮ የተገባ ነው። በዚህ ውስጥ የዚህ ዓለምም ሆነ የመጨረሻው ዓለም ስኬታችንና ድነታችን ይገኛል።

HOTLINE
+971 56 204 2045
islamicicdxb
islamicic.com
info@islamicic.com
+971 4 355 5223
DOWNLOAD AMHARIC FLYERS
www.iicdxb.com/amharic

CONTENTS




# ቁርኣን

## ለመላው የሰው ዘር የመጨረሻው ራዕይ

AMHARIC | (05/10) القرآن | FREE COPY

## መሰረታዊ ነገሮችን መማር



Dar Al Ber Society www.daralber.ae

الإمارات THE EMIRATES

Your Path To Peace..

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام

تصريح رقم: (2017/139)
دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

www.islamicic.com

CONTENTS






# ቁርኣን ምንድን ነው?

## የአላህ ቃል

ቁርኣን የአላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) ቃል ነው። በመልአኩ ጂብሪል (ሰላም በሱ ላይ ይሁን) አማካኝነት በነቢዩ ሙሐመድ (ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ላይ አውርዶታል።

"የመጽሐፉ መወረድ አሸናፊው ጥበበኛው ከሆነው አላህ ነው።"

ቁርኣን 39:1

## የሰው ልጅ መመሪያ

ቁርኣን በአጭሩ:- "ለሰዎች መሪ፣ ከቅን መንገድም ገላጮችና (እውነትን ከውሸት) የሚለይ ነው።"

ቁርኣን 2:185

ቁርኣን ለሰው ልጅ መመሪያ ዋናው ምንጭ ነው። ሰው ልክን ከሰህተት የሚለይበትን ዕድል ይሰጠዋል። ያለሱ ግን ሰው በጥፋት ወላዋይነት ውስጥ መጥፋቱ አይቀርም።

## የመጨረሻው ራዕይ

ቁርኣን የላቀው አላህ ያወረደው የመጨረሻው መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ከቀደምት ቅዱሳን መጻሕፍት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ጥቂት እውነቶችን የሚያረጋግጥና የሚያጠናክር ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ባሉት የእነዚህ ቅዱሳን መጻሕፍት ቅጂዎች ውስጥ የገቡ ውሸቶችንና ጭማሪዎችን የሚሽርና የሚያርም ነው።

"እናንተ መጽሐፉን የተሰጣችሁ ሆይ! ከእናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድነው (ቁርኣን) እመኑ።"

ቁርኣን 4:47

# ቁርኣን እንዴት እንደወረደ

ቁርኣን በነቢዩ ሙሐመድ (ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ላይ ወርዷል። እርሱም የተጠበቀ የሆነው በተወረደበት ዐረብኛ ቋንቋ ብቻ ነው። ሆኖም የመልእክቶቹ ትርጉም ግን በብዙ ቋንቋዎች ይገኛል።

ቁርኣን በአንድ ጊዜ አልወረደም። ይልቁንም የራዕይ (ወሕይ) መውረድ ሂደት ለ23 ዓመታት ዘልቋል።

በዚህ ምክንያት፣ ቁርኣንን በትክክል ለመረዳት እንዲሁም ትምህርቶቹን በተሳሳተ መንገድ እንዳንተረጉም፣ አንቀጾቹ የወረዱበትን ሁኔታ ማወቅ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ የትምህርቶቹ ትንታኔዎች ሊሳሳቱ ይችላሉ።

CONTENTS






# ቁርኣን ከአላህ መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻላል?

## ጥበቃ

ቁርኣን ለረጅም ጊዜ ሲተላለፍ የቆየ ብቸኛው ቅዱስ ጽሑፍ ነው። ከመሆኑም ጋር ከተወረደበት ቀን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ንጹህ ሆኖ ቆይቷል። ከ1400 ዓመታት በፊት ከወረደበት ጊዜ አንስቶ ምንም ነገር አልተጨመረበትም፣ ምንም ነገር አልተቀነሰበትምም። ምንም አይነት ለውጥም አልተደረገበትም።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው። እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን።”
>
> ቁርኣን 15:09

ቁርኣንን መጠብበቅ በመጽሃፍ ውስጥ ብቻ የተገደበ አይደለም። ይልቁንም በወንዶች፣ በሴቶች እና በህጻናት ልብ ውስጥም ተጠብቋል። ዛሬ፣ ቅዱስ ቁርኣን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ገጽ ድረስ በዓለም ዙሪያ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ሰዎች እንደበት ሙሉ በሙሉ ተሸምድዷል።

## የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር

ቁርኣን ከዘመናዊ ሳይንስ ጋር አይጋጭም፤ ይልቁንም ተጨባጭ እውነቶቹን ያረጋግጣል። ከትልልቅ ተአምራቶቹ ውስጥ ደግሞ እንደ ፅንስ ጥናት፣ የአየር ሁኔታ ጥናት፣ የሰነ ፈለክ ጥናት፣ የሰነ ምድር ጥናት እና የውቅያኖስ ጥናት ባሉ በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ የተፈጥሮ ክስተቶችን በትክክል የሚገልጹ በርካታ አንቀጾችን መያዙ ነው።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “እርሱም (ቁርኣን) እውነት መሆኑ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን።
>
> ቁርኣን 41:53

ሳይንቲስቶችም የቁርኣን መግለጫዎች፣ የሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጽሐፍ ቢሆንም፣ በሚያስደንቅ ሁኔታ ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

በእርግጥ በቁርኣን ውስጥ ከተጠቀሱት ብዙ የሳይንሳዊ ተአምራት አብዛኞቹ የተገኙት በቅርብ ጊዜ፣ በዘመናዊ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እድገት አማካኝነት ነው።

የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ይበሉ፦

- ቁርኣን የሰው ልጅ ፅንስ የእድገት ደረጃዎችን በዝርዝር ይገልጻል። እነዚህ ዝርዝሮች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለሳይንሳዊው ማህበረሰብ የሚታወቁ አልነበሩም።
- ዘመናዊ ሳይንስ ባህሮች በሚገናኙበት ጊዜ ውሃቸው ሙሉ በሙሉ ሳይቀላቀል የሚለያዩ የውሃ መለያዎች (Barriers) መኖራቸውን አረጋግጧል። እያንዳንዳቸውም የየራሳቸውን የሙቀት መጠን፣ ጥግግት (density) እና ጨዋማነት ይዘው ይቆያሉ።

እነዚህ የአላህ አንቀጾች ከ1400 ዓመታት በፊት በቁርኣን ውስጥ በግልጽ የተጠቀሱ ናቸው።

CONTENTS






# አቻ የለሽነት

ቁርኣን ከተወረደበት ጊዜ ጀምሮ፣ በውበቱ፣ በንግግር ምጥቀቱ፣ በአሰደማሚነቱና በጥበቡ፣ በትንቢቶቹና በሌሎችም ፍጹም መገለጫዎቹ ማንም ሰው ከአንዲት ምዕራፍ ጋር የሚመጣጠን ነገር ሊያመጣ አልቻለም።

በነቢዩ ሙሐመድ (ውዳሴና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን) የካዱ ሰዎች፣ በቁርኣን ቋንቋ እንደበተ ርቱዕ የነበሩ ቢሆንም እንኳ፣ ይህን ተግዳሮት ሊወጡት አልቻሉም። ይህ ተግዳሮት እስከዛሬም ድረስ ምላሽ ሳያገኝ ቀጥሏል።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆኑ ከብጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ። እውነተኞችም እንደሆናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ።”
>
> ቁርኣን 2:23

# መጣረስ አለመኖር

ሰዎች በሚጽፉበት ጊዜ በተፈጥሯቸው የፅህፈትና የሰዋሰው ስህተቶች፣ የንግግር መጣረሶች፣ የድምዳሜና የመረጃ አጠቃቀም ግድፈቶች፣ እንዲሁም ሌሎችም የሰው ልጅ ስህተቶችን ይፈጽማሉ።

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “ቁርኣንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ካለ ዘንድ በነበረ ኖሮ በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር።”
>
> ቁርኣን 4:82


ቁርኣን ፈፅሞ ምንም አይነት መጣረስ የለውም። ይህም በውሃ ዑደት፣ በፅንስ ጥናት፣ በሰነ ምድር ጥናት እና በኮስሞሎጂ ሳይንሳዊ ማብራሪያዎቹ ውስጥ፣ ወይም በታሪካዊ እውነታዎቹና ክስተቶቹ ውስጥ፣ ወይም በትንቢቶቹ ውስጥ ምንም አይነት ግጭት የለም።

# ነቢዩ ሙሐመድ ሊያዘጋጁት ይችሉ ነበርን?


በታሪክ ውስጥ ነቢዩ ሙሐመድ (ውዳሴና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን) ያልተማሩ እንደሆኑ ይታወቃሉ። ማንበብም ሆነ መጻፍ አይችሉም ነበር። የዚህን ታላቅ መጽሐፍ ሳይንሳዊና ታሪካዊ ትክክለኛነት እንዲሁም ስነ-ጽሑፋዊ ውበት ሊያስረዳ በሚችል በማንኛውም መስክ ትምህርት አላገኙም። በቁርኣን ውስጥ የተጠቀሱት የቀደምት ሕዝቦችና ስልጣኔዎች ታሪካዊ ዘገባዎች ትክክለኛነት ማንኛውም ሰው ሊጽፈው ከሚችለው በላይ ነው።


> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “ይህም ቁርኣን ከአላህ ሌላ የተቀጠፈ ሊሆን አይገባውም።”
>
> ቁርኣን 10:37


CONTENTS











# የራዕይ ዓላማ

## በእውነተኛ አንድ አምላክ ማመን

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው። ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው።” ቁርኣን 2:163

በቁርኣን ውስጥ በጣም አስፈላጊው ርዕስ በአንድ እውነተኛ አምላክ ማመን ነው። አምላክ ምንም አጋር፣ ልጅ፣ ወይም አቻ እንደሌለው ይነግረናል። እንዲሁም ከእርሱ ውጭ ማንም ሊመለክ እንደማይገባ ይነግረናል።

ምንም ነገር አላህን አይመስልም። ከፍጥረታቱም አንዳችም ከእርሱ ጋር አይነፃፀርም። ቁርኣን ሰብአዊ ባህሪያትን እና የሰው ልጅን ውስንነቶች ለአምላክ መስጠትን ይቃወማል።

## የሐሰት አማልክትን ሁሉ አለመቀበል

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “አላህንም ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ።” ቁርኣን 4:36

አላህ በብቸኝነት አምልኮ የሚገባው በመሆኑ፣ ከእርሱ ውጭ ያሉ ጣዖታትንና ሐሰተኛ አማልክትን መካድ ግድ ነው። ቁርኣን ደግሞ የአምላክነት መገለጫዎችን ከአላህ ውጭ ላለ ማንኛውም አካል ወይም ነገር መስጠትን ይቃወማል።

## ያለፉ ታሪኮችን መተረክ

ቁርኣን በርካታ ጠቃሚ ትምህርቶችን የያዙ ታሪኮችን ይዟል። ከእነዚህም መካከል የቀደሙት ነቢያት እንደ አደም፣ ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ዒሳ እና ሙሳ (ሰላም በነሱ ላይ ይሁን) እውነተኛ ታሪኮች ይገኙበታል።

ከእነዚህ ታሪኮች ውስጥ የላቀው አላህ እንዲህ ይላል፦

“በታሪካቸው ውስጥ ለአእምሮ ባለ ቤቶች በእርግጥ መገሰጫ ነበር።” ቁርኣን 12:111

## የመጨረሻውን ቀን ማስታወስ

“በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን። ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም።”

“በታሪካቸው ውስጥ ለአእምሮ ባለ ቤቶች በእርግጥ መገሰጫ ነበር።” ቁርኣን 21:47

## የታለመውን የሕይወት ስልት ማሳካት

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ ቁርኣን የሕይወት ዓላማ አላህን ብቻ ማምለክ እንደሆነ፣ እንዲሁም አንድ ሰው አላህ በሚወደው የሕይወት ስልት መሰረት ሕይወቱን መኖር እንዳለበት ያስተምራል።

በእስልምና አምልኮ ማለት ጠቅላይ ቃል ሲሆን፣ አላህ የሚወዳቸውን እና የሚቀበላቸውን ሁሉንም ግልጽም ይሁኑ ሰውር ተግባራትና ንግግሮችን ያካትታል።

ስለዚህ፣ ሙስሊም የአላህን ትዕዛዛት በመፈጸሙ፣ አላህን ያመልካል፤ በሕይወቱ ያለውን ዓላማም ያሳካል።

CONTENTS






ቀጥሎ ከቁርኣን የተገኙ የአምልኮ ምሳሌዎች ቀርበዋል፦

**ሰግደት:** "እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! (በሰግደታችሁ) አጎንብሱ፣ በግንባራችሁም ተደፉ። ጌታችሁንም ተገዙ። በጎንም ነገር ሥሩ፣ ልትድኑ ይከጀልላችኋልና።" ቁርኣን 22:77

**ምጽዋት መስጠት:** "ለግሱ፤ ለነፍሶቻችሁ መልካም ነውና። የነፍሱንም ንፍገት የሚጠበቅ ሰው እነዚያ እነሱ ፍላጎታቸውን የሚያገኙ ናቸው።" ቁርኣን 64:16

**እደራን መወጣት:** "እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ። እናንተም የምታውቁ ስትሆኑ እውነትን አትደብቁ።" ቁርኣን 2:42

**ትህትና:** "ለምእመናን ንገራቸው፦ ዓይኖቻቸውን (ያልተፈቀደን ከማየት) ይከልክሉ። ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ። ..." "ለምእምናትም ንገራቸው፦ ዓይኖቻቸውን ይከልክሉ። ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ።" ቁርኣን 24:30-31

**አመስጋኝነት:** "አላህም ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ። ታመሰግኑም ዘንድ ለእናንተ መስሚያን ማያዎችንም ልቦችንም አደረገላችሁ።" ቁርኣን 16:78

**ፍትሕ:** "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢሆንም እንኳ በትክክል (ፍትሕ) ቋሚዎች ለአላህ መስካሪዎች ሁኑ። ሀብታም ወይም ድሃ ቢሆን አላህ በእነርሱ (ከእናንተ) ይበልጥ ተገቢ ነው።" ቁርኣን 4:135

**ትእግስት:** "ታገስም፤ አላህ የበጎ ሠሪዎችን ምንዳ አያጠፋምና።" ቁርኣን 11:115

**በጎ ስራ መስራት:** "እነዚያንም ያመኑትንና በጎ ሥራዎችን የሠሩትን አላህ (ገነትን) ቃል ገባላቸው። ለእነርሱ ምሕረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው።" ቁርኣን 5:9

# መደምደሚያ

ባጭሩ፣ ቅዱስ ቁርኣን ሰዎችን አንድንና እውነተኛ አምላክን እንዴት ማምለክ እንዳለባቸው ያስተምራል። በዚህም በሕይወታቸው እውነተኛ ዓላማቸውን እንዲያሳኩ እና በዚህ ዓለምም ሆነ በመጪው ዓለም ስኬትን እንዲጎናፀፉ ያደርጋቸዋል።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "እኛ መጽሐፉን ባንተ ላይ ለሰዎች (ጥቅም) በእውነት አወረድነው። የተመራም ሰው ለነፍሱ ነው። የጠመመም ሰው የሚጠምመው (ጉዳቱ) በእርሷ ላይ ነው።
ቁርኣን 39:41

CONTENTS


ስለ ኢስላም አጭር ትውውቅ

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን)

መሲሑ ያመርያም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው

የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም

ቁርኣን

የህይወት አላማ ምንድን ነው?

ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች

የሴቶች መብቶች በኢስላም

የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር

ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም


# የህይወት አላማ ምንድን ነው?

AMHARIC | (06/10) الغاية من الحياة | FREE COPY

ወደ ምድር ከየት መጣሁ? ለምን ህያው ሆንኩኝ?
ከሞትስ በኋላ ወዴት ነው የምሄደው?


جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES

Your Path To Peace..

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
التعريف بالإسلام

تصريح رقم:
(2017/139)

دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

www.islamicic.com

CONTENTS






ስለ ህይወት በጥሞና ሲታሰብ የአእምሮን በር በፅኑ የሚያንኳኳው የመጀመሪያው ተቀዳሚ ጥያቄ "ከየት ተገኘን?" የሚለው ነው።

እኛ የሠው ልጆች በአንድ በድንገተኛ ተፈጥሯዊ ክስተት እንዲሁ የተፈጠርን ነን ወይንስ እጅግ ጥበበኛ የሆነ ፈጣሪ ያስገኘን ነን!? ካለመኖር ወደ መኖር የመጣንበትን የህይወት ግብና ዓላማ በቅጡ ለመረዳት የመጀመሪያው እርምጃ የፈጣሪን መኖር ማረጋገጥ ነው። የፈጣሪን መኖር የሚያስረዱ አዕምሯዊና ሎጂካዊ መረጃዎች ይገኛሉ። ከነዚህ መካከል ሶስቱን ለመጥቀስ እንሞክራለን፦

# 1. የዩኒቨርስ አፈጣጠር

ስለ ፈጣሪ መኖር የመጀመሪያ ማስረጃ የዚህን ታላቅ ዓለም የአፈጣጠር መነሻ ከመረዳት ጋር ይያያዛል።

ፀጥ ባለ ምድረ-በዳ በረሃ ላይ እየተጓዝክ እንደሆነክ አስብ። በመንገድህ ላይ ሰዓት አገኘህ። ማንም እንደሚረዳው ሰዓት ከመስታወት ከማዕድን እና ከፕላስቲክ የሚሠራ ነገር ነው። መስታወት ከአሸዋ ይሰራል። ፕላስቲክ ደግሞ ከፔትሮል ተረፈ ምርት ይገኛል። የብረት ማዕድን ከከርሰ-ምድር ይወጣል። ሰዓቱ የተሰራባቸው ሦስቱም ጥሬ እቃዎች በበርሃማው መሬት ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ሆኖ ሳለ በመንገድህ መሀል ያገኘኸው ሰዓት በዚያ በረሀ ላይ እራሱን በራሱ ያስገኘ ይመስለሀልን? ፀሀይ በምስራቅ በኩል በወጣችበት ቅጽበት በድንገት ኃይለኛ አውሎ ንፋስ ነፍሶ ከዚያም በድንገት ድፍድፉ ነዳጅ ከበረሃው መሬት ፈልቆ ከአሸዋውና ከሌሎች ማዕድኖች ጋር በመደባለቁ፤ በብዙ ሚሊዮን ዓመታት ሂደት ሰዓቱ በአጋጣሚ ተከሰተ ብትባል ታምናለህን?

> እንዳንድ ግዜ ሰይጣን "አላህን ማን ፈጠረው?" የሚል ጥያቄ ያነሳብሀል።
>
> **አላህ የሁሉ ነገር ፈጣሪ ነው። ከፍጡራኑ ይለያል። አላህ ዘልዓለማዊ ህያው ነው። ለመኖሩ መጀመሪያ የለውም። ሁልጊዜም የነበረ ነው። ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለምና ይህ ጥያቄ የተሳሳተና ንጹህ አይምሮ የማይጠይቀው ጥያቄ ነው።**

ምክንያታዊ አስተሳሰብ እና የሠው ልጅ ተሞክሮ በፍጥረተ አለሙ ያለ ነገር ሁሉ መነሻ እንዳለው ያስተምራሉ። በራሱ ኃይል ካለመኖር ወደ መኖር የሚመጣ ነገር የለም። የትኛውም ቁስ አካል ራሱን መፍጠር አይቻለውም። ስለሆነም ከዚህ በመነሳት ስለ ዓለም ልዩ አፈጣጠር አዕምሮ የሚቀበለው አሳማኝ ትንታኔ፤ ይህንን ድንቅ ዓለም

ያስገኘ ፈጣሪ መኖሩ ሲሆን፤ ይህን ታላቅ ዓለምና የሚመራበትን ድንቅ ተፈጥሯዊ ህግጋት ያስገኘ ፈጣሪ አዋቂና ጥበበኛ መሆኑ ጥርጥር የለውም። ከዚህ ግዙፍ የአፈጣጠር ጥበብ፤ የፈጣሪን ታላቅነት እንገነዘባለን። ፈጣሪ መጀመሪያና መጨረሻ እንደሌለው ከተረዳን ግዜና ቦታ ከዩኒቨርሱ መፈጠር ጋር አብረው የተገኙ ስለሆኑ ተፈጥሯዊ ህግጋታቸው አምላክን አይመለከቱም። ይህ የደረስንበት ድምዳሜ ዩኒቨርስ የተገደበ መሆኑን እና መነሻ እንዳለው ትንታኔ ከሚሰጠን ሳይንሳዊ ምርምር ጋር የተጣጣመ ነው። በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ፍሬ ሐሳቦች ስለ አላህ መኖር መሠረታዊ ግንዛቤን ያሰጨብጣሉ።

# 2. የተሟላ የአለም አፈጣጠር

የዚህን ፍጥረተ አለም ሁኔታዎች በአግባቡ ሰናጤን፤ በምድር ላይ ህይወት ይቀጥል ዘንድ ተመጥነው የተቀረፁ በርካታ ነገሮችን በግልጽ መመልከት እንችላለን። ለምሳሌ በመሬትና በፀሀይ መካከል ያለው ርቀት፣ የመሬት በተመጠነ እና አስደናቂ በሆነ ፍጥነት መሽከርከር፣ በአየር ውስጥ የሚገኘውን የኦክስጅን ምጣኔ፣ የምድራችን የላይኛው ክፍል ያለው የውፍረት መጠን፣ ወዘተ. በአጋጣሚ የተከሰቱ ሊሆኑ አይችሉም። ሁሉም የድንቅ ዕውቀት ባለቤት በሆነው ጥበበኛ ፈጣሪያችን የተመጠኑ መሆኑን መገንዘብ አይሳነንም። እነዚህ ልዩ ልዩ ተፈጥሯዊ ምጣኔዎች አነስተኛ መዛነፍ ቢከሰትባቸው ህይወት የሚባል ነገር ሊኖር

CONTENTS






አይችልም። ፀሀይ አሁን ካለችበት ርቀት ወደ መሬት ትንሽ ብትቀርብ ወይንም ትንሽ ብትርቅ፣ የኦክስጅን መጠን ካለበት መጠን ቢቀንስ፣ ወዘተ. ሁሉም ነገር ያበቃለት ነበር። በመለኮታዊ ብርሀን የተገራ አስተዋይ አዕምሮ ላለው ሠው፤ ይህ ድንቅ ዓለም ያለ ፈጣሪ ተገኘ የሚለው ንድፈ ሀሳብ ዕብደትና ጭፍንነት ነው።

የምንጠቀምበት የሰዓት መቁጠሪያ የግዜ ቅንጣቶችን በማይዛነፍ ስርዓት ይቆጥርልን ዘንድ በቂ እውቀት ያለው ባለሙያ ሊፈበርከው ይገባል። እንደዚሁ ምድር በጊዜ በተገደበ ስርዓት በጸሀይ ዙርያ ትጓዝ ዘንድ ያስቻላት ሁሉን አዋቂ ፈጣሪ መኖሩ አያነጋግርም። ይህ የምድር ጉዞ በራሷ የተቀመረ ሊሆን ይችላልን?

ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የተዘረጋውን ድንቅ ህዋ አጢነን ወደ ራሳችን ብንመለስ በሰውነታችን ውስጥ አስደናቂና ተፈጥሯዊ ስርዓቶችን እናስተውላለን። በሠውነታችን ውስጥ በአተነፋፈስ፣ በምግብ ውህደት እና በሌሎችም በርካታ ነገሮች ያለው ስርዓት- ተፈጥሮ እጅግ አስገራሚ ነው። የነገሮች ምጣኔ፣ አሰራርና አተገባበር የእውቀት ባለቤት የሆነ ፈጣሪ ስራ መሆናቸውን ያሳያል። ድንቅ ፍጥረታቱም ፈጣሪ እንዳላቸው ጮክ ብለው ይናገራሉ።

**የጥበበኛውን ፈጣሪ መኖር የሚጠቁመው ሁለተኛው ማስረጃ እጅግ ውስብስብ በሆነው በዚህ ዓለም ውስጥ የምንመለከታቸው ድንቅ ተፈጥሯዊ ህግጋትና የምናስተዉለው ረቂቅ የመመጣጠን ስርዓት ናቸው።**

# 3. መለኮታዊ መልዕክቶች

ፈጣሪ እንዳለ የሚያስረዳው ሶስተኛው ማስረጃ አላህ ወደ ነብያት ያወረደው እውነተኛው መለኮታዊ መልዕክት (ወሕይ) ነው። እነዚህ የወሕይ መልዕክቶች ሁሉንም የፈጠረው አምላካችን አላህ ለመሆኑ ድንቅ ማስረጃዎች ናቸው። የኢሰላም መሠረታዊ መጽሀፍ የሆነውን ቁርኣንን ብንመለከት ከፈጣሪ የወረደ መልዕክት መሆኑን ከሚያረጋግጡልን መረጃዎች ጥቂቶቹን ማቅረብ ይቻላል።

ለሠው ልጆች ብርሀን እንዲሆን ከአላህ የተወረደ ማንኛውም መልዕክት የአላህን ህልውና የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ሊያካትት እንደሚገባ ፈጽሞ አያጠራጥርም።

- ቁርኣን ከ1400 ዓመታት በፊት የወረደ ከመሆኑ ጋር ብዙ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ይዟል። ለምሳሌ፤ በቁርኣን በአንቢያእ ምዕራፍ ቁጥር 30 ላይ ውሀ የፍጥረታት ሁሉ መነሻ መሆኑን ይናገራል። በዛሪያት ምዕራፍ ቁጥር 48 ላይ ደግሞ ስለ ዩኒቨርስ መለጠጥ እና መዘርጋት ይናገራል። ፀሀይና ጨረቃን አስመልክቶም የየግል ምህዋሮቻቸውን ተከትለው እንደሚጓዙ ነግሮናል። “እርሱም ሌሊትንና ቀንን፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የፈጠረ ነው። ሁሉም በፈለካቸው ውስጥ ይዋኛሉ።” አልአንቢያእ 33
- እነዚህ እውነታዎች ከሳይንሳዊ እውቀት መስፋፋት ጋር በቅርብ የታወቁ እንጂ ያን ግዜ የሚታወቁ አልነበሩም።
- ከዚህ በተጨማሪ ቁርኣን በወረደበት ግዜ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የማያውቋቸውን ብዙ ታሪካዊ ዕውነታዎችን በዝርዝር አኳቷል።
- ቁርኣን በሀያ ሶስት ተከታታይ ዓመታት ቀስ በቀስ የተላለፈ እንዲሁም እጅግ ሰፊ የሆኑ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮችን የዳሠሠ ከመሆኑ ጋር በውሰጡ ፈጽሞ ከስህተትም ይሁን ከሐሳብ ተቃርኖዎች የፀዳ ነው።
- ቁርኣን ከወረደበት ጊዜ ጀምሮ በዋናው የዐረብኛ ቋንቋው ቃል በቃል ተጠብቆ ቆይቷል። ይህ ደግሞ ከሌሌሎች በዋናው ይዘታቸው ያልተጠበቁ ከሆኑ መጽሐፍት በተቃራኒ ነው።
- ቁርኣን አላህን አስመልክቶ ግልፅና ጥርት ያለ አለም አቀፋዊ መልዕክት ያዘለ ሲሆን፤ ፈጣሪን አስመልክቶ ተወራራሽ አስተሳሰቦችን እና ጥንታዊ እምነቶችን ሁሉ ይዳስሣል፤ ድክመታቸውንም ይተቻል።

CONTENTS






- ቁርኣን ሰዎች ላይ በግለሠብ ደረጃ ያለው ተጽዕኖ ጥልቅ ነው። ይህን በሚገባ መረዳት የሚችለው የቁርኣንን ልዩ ጥፍጥና በልቡ መቅመስ የቻለ ነው።
- ቁርኣን የወረደው ማንበብና መጻፍ በማይችሉት ነብይ በሙሐመድ ላይ ከመሆኑ ጋር እጅግ ውብና ምጡቅ ቋንቋዊ አገላለጾችን ይዟል። በዐረብኛ ቋንቋዊ ውበቱ እና በአገላለጹ የምጥቀት ጫፍ ስለመድረሱ በአለም አቀፍ ደረጃ ይታወቃል። መሳጭነቱም ማስረዳት ከሚቻለው በላይ ነው። ይህ ተጨባጭ እውነታ እንጂ ግነት አይደለም!!

ቁርኣን ልዩና ተዓምራዊ ይዘት ሊኖረው የመቻሉን ምስጢር ስናጤን፤ "ከአላህ ስለሆነ ነው" የሚለውን ሎጂካዊ ምክንያት እናገኛለን።

# ቀጥተኛው መንገድ

አላህ በምድር ላይ ሰንኖር ህይወታችንን በሙከራ ላይ ተንተርሰን ስህተትን የመራቅ አካሄድ ተከትለን እንመራ ዘንድ ያለመመሪያ አልተወንም። መመሪያ የሚሆነን መለኮታዊ ብርሀን ሳይልክልን እርግጠኛ ባልሆንበት የህይወት ጉዞ ብዙሀኑን በጭፍን እንድንከተል

ይተወናልን? በምድር ላይ ሰንኖር፤ ስሜታችንን እና ግላዊ ፍላጎታችን ለማሳካት ብቻ ነው ወይስ የተፈጠርንበትን መሰረታዊ ግብና አላማ አውቀን ልንተገብር? የዓለማቱ ጌታ ከእኛ የሚፈልገውን ነገርስ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

ጥበበኛ የሆነው ፈጣሪ ካልነበርንበት አዳስገኘን ሰንገነዘብ፤ ይህ ጥበበኛ ፈጣሪ ለምን እንደፈጠረን እንደሚያሳውቀን ቀጥተኛውን መንገድም እንደሚያመላክተን ልባችን እርግጠኛ ይሆናል።

አዎን! አላህ ለሰው ልጆች የተፈጠሩበትን ዓላማ እና አላህ ከእነርሱ የሚፈልገውን የአኗኗር ሰርዓት ያስረዱ ዘንዳ መልዕክተኞችን ልኳል፤ መለኮታዊ መጽሀፎችንም አውርዷል።

ባለፉት ዘመናት አላህ ብዙ ሺ መልዕክተኛ ነብያትን እንደላከና ከየህዝቡ ቢያንስ አንድ መልዕክተኛ እንዳሰነሳ ሙስሊሞች ሁሉ ያምናሉ። ሁሉም መልዕክተኞች አላህን በብቸኝነት ማምለክ እና መመሪያዎቹን መከተልን የተመለከቱ ተመሣሣይ መልዕክቶችን ይዘው መጥተዋል። ከነዚህ መልዕክተኞች መካከል ኑህ፣ ኢብራሒም፣ ሙሳ፣ ዒሳና ሙሐመድ ታላላቆቹ ናቸው፤ (በሁሉም ላይ የአላህ ውዳሴና ሰላም ይሁን።)


የዚህኛው ትውልድ ነብይ የሆኑት ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) የነብያት መደምደሚያ ናቸው። በታማኝነት፣ በፍትህ፣ በአዛኝነትና በጀግንነት በዙርያቸው ከነበሩ ሰዎች ሁሉ የላቁ ነበሩ። ከዚህ ቀደም ከአላህ የተላለፉ መልዕክቶች ለሰዎች ይብራሩ፣ አላህንም ይፈሩ ዘንድ የመጨረሻውን ከሠማይ የወረደ መልዕክት ቁርኣንን ይዘው ተነስተዋል።

ቁርኣን ቅን መመሪያን ያዘለ መጽሀፍ ነው። ብዙሀኑን ማህበረሰብ ያነጋገሩ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮችን ያብራራል። በዋነኝነት፤ የተፈጠርንለትን አላማ፣ አላህ የሚወዳቸውን እና የሚጠላቸውን ተግባራት፣ ያለፉ ነብያትን ታሪክ እንዲሁም የእለተ ትንሳኤን፣ የገነትና የገሀነምን ሁኔታዎች ያብራራል።

እንደዚሁ ቁርኣን፤ ስለ አላህ ማንነት የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ያርማል። ለምሳሌ፤ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁንና የኢየሱስን ማንነት እና ሚናቸዉን በማውሳት ከአምላክ ማንነት ጋር ያነጻጽራል።

> እንደሌሎች ነብያት ሁሉ በኢየሱስ አማካኝነትም ተአምራት ተፈጽመዋል። ሰዎች አላህን ብቻ እንዲያመልኩ ጥሪ አድርጓል። በቁርኣን በመርየም ምእራፍ ላይ ይህ አሃዳዊ የኢየሱስ ጥሪ እንደሚከተለው ተገልጿል፤ ዒሳ "አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው" አለ ።
> መርየም 36

CONTENTS
























# የኢየሱስ (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ማንነት

አንዳንድ ክርስቲያኖች ኢየሱስ አምላክ ወይም የሰላሴ አንዱ አካል ነው ሲሉ ይሞግታሉ። አምላክ በምድር ላይ በኢየሱስ መልክና ቅርፅ እንደተገለፀ ይናገራሉ። እንደ እነርሱ አባባል ኢየሱስ በሰው ልጅ ቅርጽ የተከሠተ ፈጣሪ ነው። ሆኖም በእጃቸው የሚገኘውን መጽሀፍ ቅዱስ መሠረት በማድረግ እውነታውን ስንመረምር፤ ዒሳ መወለዳቸውን፣ እንደማንኛውም ሰው መብላት መጠጣታቸውንና መተኛታቸውን፣ ብሎም ወደ አምላካቸው ፀሎት ማድረጋቸውንና የተገደበ እውቀትም እንደነበራቸው እንረዳለን። እነዚህ ፈጽሞ የፈጣሪ አምላክ መገለጫዎች ሊሆኑ እርሱንም ሊገልፁ አይችሉም!

**የመርየም ልጅ ዒሳን አስመልክቶ የሚነዙ አያሌ ብዥታዎች ከመኖራቸው አንጻር እንደ ኢስላም የፈጣሪን ማንነት ለመረዳት ስንሞክር የኢየሱስን ማንነት ጠንቅቆ ማወቁ በእጅጉ አስፈላጊ ነው**

አምላክ ልዕልናው ከፍ ያለና በመልካም መገለጫዎች የሚገለጽ ከጉድለትም የፀዳ ሲሆን የሰው ልጅ ግን ፍጡር እንደመሆኑ ጉድለት አያጣውም። ታዲያ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች በተመሳሳይ ግዜ እንዴት አንድ ሊሆኑ ይችላሉ? ይህ የመለኮታዊ መጽሀፍት መረጃዎችም ሆነ የአእምሮ ግምገማ የማይቀበለው ግልጽ ስህተት ነው።

አንዳንዶች፤ **"አምላክ ሁሉን ማድረግ የማይሳነው ከሆነ ሰው ከመሆን ምን ያግደዋል?"** የሚል ጥያቄ ያነሳሉ።

ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ እንደተረዳነው የአምላክ እና የፍጡራን ተግባራት የተለያዩ ናቸው። አምላክ ሁሉን ቻይ እና ብርቱ ሲሆን ሰው ደግሞ ብዙ ነገሮች የሚሳኑት ደካማ ነው። ስለዚህ ጥያቄው እርስ በርሱ የተምታታ ነው። "አምላክ ሁሉን ቻይ ብርቱ ከሆነ፤ ለምን ነገሮች የሚሳኑት ደካማ ፍጡር አልሆነም?" እንደማለት ሲሆን "ሁሉን ቻይ ከሆነ" ከሚለው መነሻ ጋር በቀጥታ ይጋጫልና ጥያቄው ከመሰረቱ ውድቅ ነው። አምላክ የፍጡራን መገለጫ የሆኑ የጉድለት መገለጫዎችንና ተግባራትን አይጋራም። አምላክ ማንነቱን ቀይሮ ከፍጥረታቱ አንዱን ከሆነ፤ የፍጡርንም ጉድለትና ደካማነት ከተላበሠ አምላክ አልሆነም!!

ዒሳ ለተከታዮቻቸው "እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ" አሉ እንጂ "እኔ አላህ ነኝ" በማለት አላስተማሩም። ክንዋኔዎቻቸውንም ሲያደርጉ የነበረው እንደ አንድ ለፈጣሪ ታዛዥ ፍጡር እንጂ እንደ ፈጣሪ አልነበረም። በኢንጅል (ወንጌል) ውስጥ ይህን ሐሳብ የሚጠቁሙ ብዙ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል።

ለምሳሌ ያህል በማቲዎስ ወንጌል (26:39) ላይ ኢየሱስ በግንባሩ ተደፍቶ በመሰገድ እንደፀለየ ተገልጿል።

**ኢየሱስ አምላክ ከሆነ፤ በግንባሩ ተደፍቶ መፀለዩን ንጹህ አይምሮ ይቀበለዋልን? ኢየሱስ የሰገደለት አምላክስ ማን ነበር?**

**አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ኢየሱስ የአምላክ ልጅ ነው ይላሉ። ይህ ምን ማለት ነው? ፍጡራን በሚኖራቸው መልኩ ልጅ ሊኖረው ፈጽሞ አይቻልም። አምላክ ከዚህ በእጅጉ የላቀ ነው። ታዲያ አምላክ ልጅ አለው ሲባል ምን ማለት ይሆን?**

**"ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም:: (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ::"**

ቁርኣን 19:35

የመጽሀፍ ቅዱስን አገላለጽ ስናጤን፤ በቀጥተኛ ትርጓሜ ፈንታ "የአምላክ ልጅ" ለሚለው ገለጻ ዘይቤያዊ ትርጓሜ "ቅዱስ የአምላክ ባሪያ" ለማለት ሲያገለግል እናያለን። ይህም ሲሆን በዚሁ መጽሀፍ ውስጥ ይህንን ገለጻ ለኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ለዳዊት ለሠለሞን እና ለያዕቆብ ሲጠቀም እናያለን። ልጅ የሚለው ገለጻ ጻድቃንን ሁሉ ለማመልከት አገልግሏል። ለምሳሌ ያህል እንዲህ የሚለውን መውሰድ እንችላለን:- "እስራኤል (ያዕቆብ) የበኩር ልጄ ነው።" (ዘፀዓት 4:22) ሆኖም በዚህኛው ዘይቤያዊ ትርጓሜም ቢሆን የአምላክ ልጅ በሚል መግለጽ በራሱ ለተሳሳተ ግንዛቤ ሊያበቃ ይችላልና ተቀባይነት የለውም። በቅዱስ ቁርኣን ይህንን አጠቃቀም የሚያወግዙ በርካታ አንቀጾችን እናገኛለን።

CONTENTS






ኢስላም የፈጣሪን ታላቅነት እና ብቸኛ ተመላኪነት እንዲሁም የአላህን ምሉእነት በግልጽ ከማስተማሩ ጋር እውነተኛውን የዒሳ ማንነትም ጥርት ባለ መልኩ አስቀምጧል። ዒሳ ለህዝባቸው የአላህን መልዕክት እንዲያስተምሩ የተላኩ የአላህ ታዛዥ መልዕክተኛ ናቸው።

# ስለዚህ ለምን በዚህ አለም እኖራለሁ?

አይን፣ ጆሮ፣ አይምሮና ልብን የመሳሰሉ የሰዉነት ክፍሎችን ብንመለከት የመኖራቸው አላማ ግልጽ ነውና ሁሉም ሰው እንደዚሁ የነዚህ የሰውነት ክፍሎች ሰብሰብ የሆነው ሰው ለመኖሩ ግልጽ አላማ አለው!

ጥበበኛው አላህ ያለ ምንም ግብና ዓላማ ህይወታችንን እንድንገፋ አልፈጠረንም። የመገኘታችን ምስጢር በመብላት በመጠጣትና ከተቃራኒ ጾታ እርካታ በማግኘት ብቻ የታጠረ አይደለም። ለዚህ አልተፈጠርንም!

የተፈጠርንበት ዓላማ፣ በምድር ላይ የተገኘንበትም ታላቅ ግብ አለ። እርሱም አላህ እንዳለ ማረጋገጥና እርሱን ብቻ ማምለክ ነው። አላህ ባሰቀመጠልን የብርሃን መንገድ ህይወታችንን ስንመራ በሁሉም የህይወት መስኮች ስኬታማና ደስተኞች እንሆናለን። እርካታ ለኛ ቅርብ ይሆናል። ይህም መመሪያ እንደ ሶላት ያሉ ግላዊ አምልኮቶችን ያካትታል። እንደዚሁ ለጎረቤት መልካም መዋል፣ ለቤተሰብና ለእንስሣት እንክብካቤ ማድረግን የመሰሉ ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙ ተግባራትን ያካትታል።

አላህ ከእርሱ ውጭ የሚገኙ እንደ ጣኦታትን፣ ጸሀይና ጨረቃን፣ ጻድቃንና ነብያትን ማምለክ እርም አድርጎብናል። አላህ ተጋሪ የለውም። አማላጅ እና ባሪያውን ከርሱ ጋር የሚያገናኝ መዳረሻ አያስፈልገውም። አላህን ብቻ በማምለክ ማንኛውም ፍጡር ወደ አላህ መድረስ ይቻለዋል።

ምድራዊ ህይወት የሰው ልጆች የሚፈተኑበት የፈተና ሀገር ነው። የሰው ልጅ በህይወት ጉዞው ውስጥ ብዙ ፈተናዎች ያጋጥሙታል። በህይወታችን ውስጥ የሚፈጠሩ ነገሮችን

መቆጣጠር አንችልም። ነገር ግን ለህይወት ክስተቶች የምንሠጠውን ግብረ መልስ መምረጥ እንችላለን። ወደ አላህ ከሚያቃርቡን ተግባራት መካከል በመከራ ወቅት ትዕግስትን መላበስና ስለ ጸጋዎቹም አላህን ማመስገን ይገኙበታል። እነዚህ ጀነት ለመግባት የሚረዱ ምክንያቶች ናቸው። በአንጻሩ በፈጣሪ ካላመንን እና ለትዕዛዛቱ ዕንቢተኛ ከሆንን የእሳት ቅጣት እንሚጠብቀን አላህ አስጠንቅቆናል።

# ምን ማድረግ አለብኝ!?

የአንድ ሰው እምነት የሚፈተሸው፤ ምርጫውን ፈቃዱን እንዲሁም የማስተንተን ችሎታውን በመጠቀም፤ ጥበበኛ ፈጣሪ የሆነ አምላክ እንዳለው ሲጠቁሙት ነው። ይህ ደግሞ የሚፈጸመው ለአላህ ትዕዛዛት እጅ ስትሰጥ ብቻ ነው። ይህም በዐረብኛ ቋንቋ "ሙስሊም መሆን" ማለት ነው።

ኢስላም ለሁሉም የሰው ዘር በሩ ክፍት ነው። ያለፈ የማንነት ታሪክና እምነት፣ ወይም የሚኖሩበት የኑሮ ደረጃ ተጽዕኖ አይፈጥሩም። ማንኛውም ሠው በቀላሉ የአላህን ብቸኛ ተመላኪነትና የሙሐመድን መልዕክተኛነት በልቡ በማመን እና በአንደበቱ በመመስከር

ሙስሊም ሊሆን ይችላል። ሙስሊም የምትሆንበት የምስክርነት ቃል ይህ ነው፦

**“አሽሀዱ አላ-ኢላሀ ኢለላህ ወአሽሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉላህ!”**

**“ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው እውነተኛ አምላክ እንደሌለ፤ ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”**

የፈጣሪን መኖር አምነህ የተፈጠርክበትን አላማ ለመፈጸም ተግተህ የምትሰራበት ግዜ አልደረሰምን? በምድር ላይ ያለህ ቆይታ ምን ያክል እንደሆነ አታውቅምና ይህንን የምስክርነት ቃል በመመስከር በምድራዊውና በመጭው ዘልዓለማዊ አለም ስኬትን የምታገኝበት ግዜ አሁን መሆን ይኖርበታል!

CONTENTS

ስለ ኢስላም አጭር ትውውቅ
ነብዩ ሙሐመድ
መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው
የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም
ቁርኣን
የህይወት አላማ ምንድን ነው?
ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች
የሴቶች መብቶች በኢስላም
የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር
ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም

# ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች

AMHARIC (07/10) مفاهيم خاطئة حول الإسلام FREE COPY

ስለ ኢስላም የምታወቀው ትክክለኛ መረጃ ምን ይሆን?

جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES

Your Path To Peace..

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
التعريف بالإسلام

www.islamicic.com

تصريح رقم:
(2017/139)
دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

CONTENTS






# መግቢያ

ኢስላም በምድር ላይ በከፍተኛ ደረጃ ከተስፋፉ ሀይማኖቶች መካከል ቢሆንም በብዙ ምክንያቶች ሰዎች በተዛባ መልኩ የተገነዘቡት ሀይማኖት ነው። ለዚህም ርካሽ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማሳደድ ወይም ከፅንፈኛ ጥላቻ በመነሳት ኢስላምን በመጥፎ የሚስሉ ሚዲያዎች ታላቁን ድርሻ ይወስዳሉ። ባዶ ስጋትና ፍርሀት የወለዷቸው የተዛነፉ ግንዛቤዎችም ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው። ስለ ኢስላም እና ስለ ሙስሊሞች ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት የሚቻለው፤ የተዛቡ ምልከታዎችን በመራቅ በእያንዳንዱ ርዕስ ጉዳይ ላይ ትክክለኛ ኢስላማዊ ምንጮችን መሰረት ያደረገ ግምገማ ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው።

> "ከእናንተ መካከል መልካም ማለት ፀባዩ ያማረ ሰው ነው።"
>
> ቡኻሪይ 3559

## የተዛባ ግንዛቤ 1 – “ሙስሊሞች ሙስሊም ላልሆኑ ሰዎች መልካም ነገር አይመኙም በጎም አይውሉም።”

አንዳንዶች፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ማህበራዊ እሴቶች ኢስላም ውስጥ የሉም ሙስሊሞችም አያከብሯቸውም በማለት ይተቻሉ። ሆኖም ይህ ትችት ፍጹም ከመረጃ እና ከፍትህ የራቀ ነው።

ነብዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦

- ታማኝና ፍትሀዊ እንድትሆን፣
- ቀጠሮ እንድታከብር፣
- በሰዎች እምነት እንዳትሳለቅ ይከለክልሀል፣
- ወላጆችህን እንድትታዘዝ፤ ለዘመዶችህ፣ ለጎረቤቶችህና ለታላላቆችህ ክብር እንድትሰጥ ያዛል።
- ኢስላም፤ በጎ አደራጊ እንድትሆን ለድሆችና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ ትኩረትና እንክብካቤን እንድታደርግ፣
- ከጎረቤቶችህ ጋር መልካም ግንኙነትን እንድታዳብር ይገፋፋሀል።
- ከውሸት፣ ከማጭበርበር፣ ሰዎችን ከመዝለፍና ከሀሜት ይከለክልሀል።

ሙስሊሞች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ አወንታዊ ሚና ይኖራቸው ዘንድ፤ መልካም ባህሪንና ስነ ምግባርን እንዲላበሱ ሰብዕናቸውን በጥሩ ንግግርና ተግባር እንዲገነቡ ታዘዋል።

> በመሠረቱ ሙስሊሞች የሚያመልኩት እንደ ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳና ዒሳ ያሉ ነብያት ያመለኩትን አምላክ ብቻ ነው።

## የተዛባ ግንዛቤ 2 – "ሙስሊሞች ‘አላህ’ የሚባል አዲስ አምላክ ያመልካሉ"

"አላህ" የሚለው ቃል በዐረብኛ ቋንቋ አምላክን የሚጠቁም ሲሆን ይህ ቃል ታላቅ ትርጓሜ ያለው በመሆኑ ለአንዱ አምላክ እንጂ ለማንም የሚሰጥ ስያሜ አይደለም። የዐረብ አይሁዶች እና ክርስቲያኖች አምልኮ የሚፈጽሙለትን አምላክ ለማመላከት የሚጠቀሙበት ስያሜ ነው።

ሙስሊሞች፣ አይሁዶችና ክርስቲያኖች በአንድ ፈጣሪ አምላክ ቢያምኑም ነገር ግን ስለ አምላክ ማንነት ያላቸው ግንዛቤ እጅግ ሰፊ በሆነ መልኩ ይለያያል። ለምሳሌ፤ ሙስሊሞች የፈጣሪን ሰው ሆኖ መወለድ እና ፈጣሪ ልጅ አለው የሚሉትን አስተሳሰቦች ይነቅፋሉ። አምላክ የሰላሴ ጥምረት አካል መሆኑንም አይቀበሉም። አምላካቸውን ሙሉዕ በሆኑ መገለጫዎች ብቻ ይገልፁታል።

CONTENTS






## የተዛባ ግንዛቤ 3 – "ኢስላም ሽብርን ያበረታታል"

ወገንተኛ ሚዲያዎች ማንኛውንም ተዋጊ ሙስሊም ዘወትር ሽብርተኛ ይሉታል። በዳይም ይሁን ተበዳይ፣ በፍትህዊና ህጋዊ ምክንያት ይታገልም አይታገልም ሽበርተኛ ይሉታል።

ኢስላም ግልጽ በሆነና ፍንትው ብሎ በሚታይ መልኩ ተዋጊ ያልሆኑ ሰላማዊ ሰዎችን ኢላማ ማድረግና ጥፋትን ማድረስ በጦርነት ጊዜም ቢሆን ይከለክላል። እንደ እውነታው ከሆነ ኢስላማዊ አስተምህሮ የሙስሊሙን ህልውና ለመፋቅ ሰይፋቸውን ከመዘዙ ጠላቶች ጋር በሚደረግ የጦር ሜዳ ፍልሚያ ላይ እንኳ እንስሳትና እጽዋትን ከማጥፋት ይከለክላል። ሠላማዊ ሠዎችን አስመልክቶም ክልክልነቱ የከበደ መሆኑ አያጠራጥርም።

ሆኖም ግን በሽብርና ወረራን ለመከላከል በሚደረግ የነጻነት ትግል መካከል ያሉ ልዩነቶችን ማጤን ግድ ይለናል። በመካከላቸው ያለው ልዩነት በጥቁርና በነጭ ቀለሞች መካከል ያለውን ያህል የጎላ ነው።

ምንም በማያጠራጥር መልኩ ቁርኣን ንፁህን ነፍስ ማጥፋትን ይከለክላል። የሰው ልጅ ህይወት ያላትን ክብርም ያሰምርበታል።

**የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "እነሆ! ነፍስን በመግደል ወይም በምድር ላይ በማጥፋት (ምክንያት ካልሆነ በስተቀር) ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ማለትን ጻፍን።"**

ቁርኣን 5:32

## የተዛባ ግንዛቤ 4 – "ኢስላም ሴቶችን ይጨቁናል"

እንደ ኢስላም፤ ወንዶችና ሴቶች በአላህ እይታ እኩል ናቸው። ስለ ስራቸው ሂሳብ ከመደረግ፤ ብሎም ለታላቅ ስኬትና ምንዳ ከመብቃት ወይም ለከባድ ቅጣት ከመዳረግ አንፃር ልዩነት የላቸውም። አላህ ዘንድ አንዱ ከሌላው ብልጫ የሚያገኘው ለትዕዛዛት ክብር ከመስጠትና እርሱን ከመፍራት አንጻር ብቻ ነው።

የየላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦
**"አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው።"**

ቁርኣን 49:13


ይህ አንቀጽ እንደሚያስረዳው ትክክለኛው ክብር የሚገኘው በድህነት ወይም በሀብት፤ በቆዳ ቀለም ንጻትና ጥቁረት ሳይሆን፤ ወንድም ይሁን ሴት ለአላህ ባላቸው ፍራቻና የእምነት ጥንካሬ ብቻ የሚወሰን ነው።

አላህ ወንዶችና ሴቶችን ሲፈጥራቸው አካላዊ፣ አዕምሯዊና ስነልቦናዊ የተፈጥሮ ይዘታቸውን የሚመጥኑ ሀላፊነቶችና ሚናዎችን ለይቶላቸዋል። አቅምን ያገናዘበ ተጠያቂነትንም ጥሎባቸዋል።

**አላህ ወንዶችና ሴቶችን ሲፈጥራቸው አካላዊ፣ አዕምሯዊና ስነልቦናዊ የተፈጥሮ ይዘታቸውን የሚመጥኑ ሀላፊነቶችና ሚናዎችን ለይቶላቸዋል። አቅምን ያገናዘበ ተጠያቂነትንም ጥሎባቸዋል።**

ኢስላም ለሴት ልጅ ተገቢውን ክብር ችሯል። ባማረ መልኩም ክብሯን አልቆታል። እኩልነተ ፍትህ በሚሆኑበት ሁኔታዎች ሁሉ እኩልነትን አጎናጽፏታል። ለስራዋ ክፍያን ማግኘቷ፣ ለጋብቻ ፍቃድና ምርጫዋ መከበሩ፣ ትምህርቷን መሟሯ፣ የፍቺ ጥያቄ ማቅረቧና የውርስ ድርሻዋን የማግኘት መብቷ መከበሩ ለዚህ ምስክሮች ናቸው።

CONTENTS
























እጅግ የሚያሳዝነውና የሚያስቆጨው ግን፤ አንዳንድ ሙስሊም ሴቶች የጭቆና ሰለባ መሆናቸው ነው። ይህ ግን በኢሰላም እና በአስተምህሮቱ ምክንያት የሚከሰት አይደለም። የኢሰላም እንከን ሳይሆን በአንዳንድ ሀገራት የሚገኙ ማህበረሰቦች ልማድና ባህል ነው። ይህ ደግሞ እንደ ኢሰላም ተቀባይነት የለውም።

## የተዛባ ግንዛቤ 5 – "ቁርኣን የታሪክ ወይም የግጥም መጽሀፍ ነው"

ክቡሩ ቁርኣን የአላህ ንግግር ነው። አላህ በጂብሪል አማካኝነት ወደ ነብዩ ሙህመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) አስተላልፎታል። ቁርኣን እውነትና ሀሰትን ገላጭ መለያ ነው። የሠው ልጆች ስኬታማ የሚሆኑበትን ቅን መንገድ የሚያመላክት መጽሀፍ ነው።

ቁርአን ምን እንደሚያስተምር ለመገንዘብ ተመራጩ መንገድ በእራስዎ ቁርአንን ማንበብዎ ነው።

ካለፉ ነብያትና ከህዝቦቻቸው የህይወት ተሞክሮ እንወሰድ ዘንድ ከታሪካቸው የሚቀሠሙ ትምህርቶችን አንጥሮ ያሳየናል።

እንደዚሁ ቁርኣን ስለ ፈጣሪያችን አላህ ስለ አፈጣጠራችንና ስለ ተፈጠርንበት አላህን ብቻ የማምለክ አላማ ያስረዳናል።

አላህ የሰው ልጆችን የፈጠራቸው ካለ አላማ እንዲዋልሱ አልነበረም፤ ካለምንም ትዕዛዝና መመሪያ እንዲሁ የሚተዋቸውም አይደለም። የአንድ ሰው እምነት የሚፈተሸው፤ ምርጫውን ፈቃዱን እንዲሁም የማስተንተን ችሎታውን በመጠቀም፤ ጥበበኛ ፈጣሪ አምላክ እንዳለው ሲጠቁሙት ነው። ይህም እውነታ ግልጽ ይሆንለት ዘንድ አላህ ምልክቶችን እንደላከለት ሲገነዘብም ነው። አላህ ቁርኣንን ማውረዱም ከነዚህ ገሳጭ ተዓምራት መካከል ነው።

ቁርኣን በራሱ ብዙ ተዓምራትን ያቀፈ መሆኑ፤ ከሰማያትና ከምድር አምላክ የተወረደ ስለመሆኑ ቅንጣት ታክል ጥርጥር እንዳይኖር ያደርጋል።

ቁርአን ምን እንደሚያስተምር ለመገንዘብ ተመራጩ መንገድ በእራሰዎ ቁርአንን ማንበብዎ ነው።

## የተዛባ ግንዛቤ 6 – "ሒጃብ ጭቆና ነው"

የሒጃብን ምንነት እንድንረዳ ተከታዮቹን ነጥቦች እናስተውል። ሙስሊም ሴቶች ሰውነታቸውን በልብስ እንዲሸፍኑና ውበታቸውንም ለባዕድ ወንዶች ግልጽ እንዳያደርጉ ታዝዋል።

ነገር ግን ሒጃብ ውጫዊ ገጽታን ብቻ የተመለከተ አይደለም። ሂጃብ ውስጥንም ይመለከታል። መልካም ንግግር፣ ጨዋነትና የመጠቀ ስነ ምግባር የሂጃብ አንኳር መገለጫዎች ናቸው።


ሒጃብ አያሌ ጥቅሞች ቢኖሩትም ሙስሊም ሴቶች ሒጃብን እንዲለብሱ የሚያደርጋቸው ዋነኛው ምክንያት ግን የአላህ ትዕዛዝ መሆኑ ነው። አላህ ለፍጥረታት የሚበጀውን ሁሉ ያውቃልና።

ሒጃብ ለሴት ልጅ በውጫዊ አካላዊ ገጽታዋ ምትክ የውስጥ መንፈሳዊ ውበቷን ያጎላል። ሴት ልጅ ክብሯንና ጨዋነቷን ጠብቃ በምትኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ጉልህ ሚና ይኖራት ዘንድ የሚያስችል ነጻነት ያጎናጽፋታል።

ሒጃብ የጭቆና፣ የበደልና የማዕቀብ መገለጫ አይደለም። ይልቁንም ሒጃብ እንድን ሴት ከጎጂ እይታዎችና ከስሜት ተከታይ ወንዶች ትንኮሳ እንዲሁም ከዘረኝነት ጽንፎች ይጠብቃታል።

ሙስሊም ሴት ሂጃብ ስትለብስ ውጫዊ አካሏ እንጂ አይምሮዋና የማስተዋል ብቃቷ እንዳልተሸፈነ ሊታወቅ ይገባል።

CONTENTS


























## የተዛባ ግንዛቤ 7 – "ኢስላም የዐረቦች ብቻ ሀይማኖት ነው"

አንዳንዶች ዐረብ ያልሆኑ ሰዎች ኢስላምን ሲቀበሉ፤ ማንነትን መካድ አስመስለው በማቅረብ ኢስላም የዐረቦች ብቻ የሆነ ያክል ለማሸማቀቅ ይሞክራሉ። እውነታው ግን ይህ አይደለም። ዐረቦች ከሙስሊሙ ማህበረሰብ 20% ብቻ ሲሆኑ 80% ሙስሊሞች ዐረብኛን አይናገሩም። ግልጽ ለማድረግ ያክል በህንድና በኢንዶኔዥያ የሚገኙ ሙስሊሞች ቁጥር ብቻ ከሁሉም ዐረብ ሙስሊሞች ቁጥር ይልቃል።

ከኢስላም አስተምህሮቶች መካከል የዘር መድሎን መዋጋቱ ተጠቃሽ ሲሆን ማንም ሰው በዘሩ ወይም በቀለሙ ከሌላው ሰው ብልጫ አያገኝም። ኢስላም ለሠው ዘር በሙሉ አለም አቀፋዊ መልዕክት ነው። አዎን! ማንም ሠው በመጭው አለም እውነተኛ ስኬትን የሚያገኘው አላህን ብቻ በማምለክ መመሪያውን ሲከተል ብቻ ነው።

## የተዛባ ግንዛቤ 8 – "ጂሀድ ሽብር ነው"

ጂሀድ ማለት አምላካዊ ድንጋጌዎችን ባልተቃረነ መልኩ የሚፈጸም ትግልና መስዋዕትነት ነው። "ጂሀድ" የሚለው ቃል፣ መከላከል፣ ትዕግስት ማድረግና መጽናትን የሚያመለክት ሲሆን፤ መልካም ስራዎችን እንዲሁም የበጎ አድራጎት ልገሳዎችን ሁሉ ይመለከታል። ጂሀድ ስንል፤ የግል ሀይል ስሜትን፣ መጥፎ ዝንባሌን፣ ሰይጣን እና አጥፊዎችን በልብ በአንደበት እና በተግባር መታገል ነው። ሆኖም ብዙዉን ግዜ ጂሀድ ሲነሳ የሚታወሰው፤ የሰዎችን ሰላምና መረጋጋት ለማረጋገጥ ፍትህን በማንገስ በደልን፣ ጭቆናንና ጥቃትን ለማስቆም የተደነገገውን የመከላከል ወይም የማጥቃት ወታደራዊ የጂሀድ ትግል ብቻ ነው።

## የተዛባ ግንዛቤ 9 – “ሙስሊሞች ሙሀመድን ወይም ጨረቃን ያመልካሉ”

ሁሉንም ነብያት ማክበር ከኢስላም ዋና ዋና አስተምህሮቶች መካከል ነው። ነገር ግን እነሱን ማክበርና መውደድ ለነሱ አምልኮ መፈጸም አይደለም።

ሌላው የተዛባ አመለካከት ሙስሊሞች ነብዩ ሙሐመድን ያመልካሉ የሚለው ሲሆን እውነታውን በግልጽ የሚጻረር ሆኖ እናገኘዋለን። ተከታዩ ነብያዊ አስተምህሮ ይህንን ትችት ውድቅ ለማድረግ በቂ ነው። "ክርስቲያኖች የመርየም ልጅ ዒሳን በማወደስ ድንበር እንዳለፉ ሁሉ እኔንም ድንበር ባለፈ መልኩ አታልቁኝ። እኔ የአላህ አገልጋይ ባሪያና መልክዕተኛ ብቻ ነኝ።" (ቡኻሪይ: 3445) ሁሉንም ነብያት ማክበር ከኢስላም ዋና ዋና አስተምህሮቶች መካከል ነው። ነገር ግን እነሱን ማክበርና መውደድ ለነሱ አምልኮ መፈጸም አይደለም።

ሌላም ከእውነታውና ከተጨባጩ ጋር የሚጻረር ትችት ሙስሊሞች ጨረቃን ያመልካሉ የሚለው ነው። እንደ ኢስላም ፀሀይንም ይሁን ጨረቃን ወይም ሌላ ማንኛውንም ከአላህ ውጭ ያለ ነገር ማምለክ ሺርክ የሚሰኝ ሲሆን በእጅጉ የተከለከለና ምህረት የሌለው ኢስላምንም የሚያበላሽ ነው።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው። ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ። ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ። እርሱን ብቻ የምትግገዙ ከሆናችሁ (ለሌላ አትስገዱ።)"

ቁርኣን 41:37

ኢስላም የፈጣሪን ታላቅነት፣ ሙሉዕነትና ብቸኛ ተመላኪነት ያረጋግጣል። አላህ አዛኝና ፍትሀዊ አምላክ ነው። አላህን በብቸኝነት ማምለክ አንድነቱንም ማረጋገጥ የኢስላም አስኳል መልዕክት ነው። ይህም በቁርኣን እና በነብዩ አስተምህሮቶች ውስጥ በሰፊት ተዳሷል።

CONTENTS






## የተዛባ ግንዛቤ 10 – "ኢስላም የግዴታ ጋብቻን ይፈቅዳል"

በተለያዩ ሀገራት ከአካባቢው ልማዳዊና ባህላዊ ሁኔታዎች አንጻር የጋብቻ አፈጻጸም ስርዓቶች ይለያያሉ። በልማድ የግዴታ ጋብቻን የሚፈቅዱ ሰዎች ወይም ጎሳዎች ሙስሊሞችም የሌላ እምነት ተከታዮችም ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ጸረ-ኢስላም ጽንፈኞች በመጥፎ አላማ ጉዳዩን ከኢስላም ጋር ብቻ ለማዛመድ ይሞክራሉ።

ኢስላም ለወንድም ይሁን ለሴት የጋብቻ ምርጫን የመቀበልም ይሁን ያለመቀበል ምርጫ ይሰጣል።

ነብዩ ሙሀመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "ቀደም ሲል አግብታ የፈታች ሴት ከተጠሪ ቅርብ ዘመዷቿ ይበልጥ ስለ ራሷ መብት አላት። ልጃገረድም ፈቃድ ትጠየቃለች። ዝምታዋ ስምምነቷን ያሳያል።" (ሙስሊም፡ 1421)

ሴት ልጅ በግዴታ የምትዳር ብትሆን ኖሮ "ፈቃድ ትጠየቃለች" የሚለው አስተምህሮ ትርጉም ያጣ ነበር።

## የተዛባ ግንዛቤ 11 – "ኢስላም ሰዎች ሙስሊም ይሆኑ ዘንድ ያስገድዳል"

ሙስሊሞች ውብ የሆነውን ሀይማኖታቸውን በማስተዋወቅ ሌሎችን መጋበዝ ግዴታቸው ነው። ማስገደድን በተመለከተ ግን ማንም ሠው ኢስላምን እንዲቀበል ሊገደድ አይፈቀድም። ኢስላማዊ እምነትን መያዝ በአላህ ማመንና እርሱንም መታዘዝ በሙሉ ፍቃደኝነትና ሙሉ ነጻነት ብሎም እርግጠኝነት የመነጨ መሆን አለበት። ስለዚህ ማንንም ሰው ኢስላምን በመቀበል ላይ ማስገደድ አይቻልም።

> አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) እንዲህ ብሏል፦
> **በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ።"**
> ቁርኣን 2:256

ተከታዬቹን ነጥቦች ያስተውሉ፦

- በዓለም ላይ ከፍተኛው የሙስሊሞች ቁጥር የሚገኝባት ኢንዶኔዢያ ኢስላም የደረሰው ካለምንም ጦርነት አንድም ጠብታ ደም ሳይፈስ ነው።
- በዐረቢያ እምብርት በግብፅ ለብዙ ምዕተ ዓመታት የኮፕቲክ ክርስቲያኖች የኖሩ ሲሆን ቁጥራቸው 14 ሚልዮን ደርሷል።
- ባሁኑ ጊዜ ኢስላም በምድራችን ላይ ካሉ ሀይማኖቶች ሁሉ ፈጣን እድገት ያለው ሀይማኖት ነው።
- እንደ ኢስላም፤ ችግርና በደልን በማስወገድ ፍትህን ማንገስ ጂሀድን ለማወጅ በቂ ምክንያቶች ቢሆኑም ኢስላምን ተገደው እንዲቀበሉ ማድረግ ግን ከነዚህ ህጋዊ የጂሀድ አላማዎች ውስጥ አይመደብም።
- ሙስሊሞች ስፔይንን ለስምንት ምዕተ ዓመታት አስተዳድረዋል። ነገር ግን ሀይማኖታቸውን በግዴታ እንዲተገብሩ አላስገደዱም።

## መደምደሚያ

ኢስላምን ለመግለጽ ብቁ ካልሆኑ አካላት ወይም ካልታመኑ ምንጮች ሳያረጋግጡ ስለ ኢስላም መማር ለብዙ የተዛቡ ግንዛቤዎችና እይታዎች ይዳርጋል። 1/4 የአለም ነዋሪዎች የሚከተሉት ይህ ታላቅ ሀይማኖት አንዳንድ ወገንተኛ ሚዲያዎች እንደሚያጠለሹት ሳይሆን እጅግ ውብ ሀይማኖት ነው። ከትክክለኛ ምንጮች ሳያመሳክሩ በተዛቡ ግንዛቤዎችና በሸውራራ እይታዎች አመለካከትዎን እንዳይበክሉ አደራ እንላለን።

ኢስላም የሠላምና የእዝነት ሀይማኖት ነው፤ ተልዕኮውም በትኩረት ሊጠናና በጥልቀት ሊታይ አስተዋይነት በተሞላበት መልኩም ሊገመገም ይገባዋል። አሉታዊ አቋም ከመያዝና ፍርድ ከመስጠት በፊት ይህን ማድረግ ግዴታ ነው።

CONTENTS




# የሴቶች መብቶች በኢስላም

AMHARIC | (08/10) حقوق المرأة في الإسلام | FREE COPY

## ሴት ልጅ የታፈረች፣ የተከበረች፣ የከበረች ነች።

جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES

Your Path To Peace..

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام

تصريح رقم:
(2017/139)
دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

www.islamicic.com

CONTENTS






# መግቢያ

በእስልምና ሴት ባሪያ፣ የተዋረደችና የተጨቆነች እንደሆነች የሚያስቡ አሉ። ግን እውነት እንደዛ ናትን? በሚሊዮን የሚቆጠሩት ሙስሊም ሴቶች እንዲሁ ባሪያዎች ናቸውን? ወይስ እነዚህ የተሳሳቱ አመለካከቶች በተዛባ የመገናኛ ብዙኃን ቅስቀሳ የተፈጠሩ ናቸው?

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “እነርሱም (ለሴቶች) የዚያ በእነርሱ ላይ ያለባቸው (ግዴጅ) ብጤ በመልካም አኗኗር (በባሎቻቸው ላይ መብት) አላቸው።”
>
> ቁርኣን 2:228

ከአስራ አራት መቶ ዓመታት በፊት፣ ኢስላም ለሴቶች በምዕራቡ ዓለም ሴቶች በቅርብ ጊዜ ብቻ ያገኟቸውን መብቶች ሰጥቷቸዋል።

በ1930ዎቹ ዓመታት ውስጥ አኒ ቤሳንት የሚከተለውን ወሳኝ እውነታ ተናግራለች፦ "ክርስቲያናዊቷ እንግሊዝ ለሴቶች የንብረት መብትን ያፀደቀችው በቅርብ ጊዜ ነው። ኢስላም ግን ይህን መብት በሁሉም ዘመናት አረጋግጦላቸዋል። ኢስላም ሴት ነፍስ የላትም የሚል ሰብከት አለው ማለት ግልፅ ቅጥፈት ነው።" [ሙሐመድ፣ ህይወቱ እና አስተምህሮው፣ 1932]።

ወንዶችና ሴቶች ሁሉም የተገኙት ከአንድ ሰው ነው። እርሳቸውም ነቢዩ አደም (ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን) ናቸው። ኢስላም ከሁለቱም ወገን የሚቀበለው ፍትህንና መልካም አያያዝን ብቻ ነው።

# እኩል ምንዳ እና እኩል ተጠያቂነት

ወንዶችና ሴቶች አላህን በተመሳሳይ መንገድ ያመልካሉ። ማለትም ያንኑ አንድ አምላክ ነው የሚያመልኩት። ተመሳሳይ የአምልኮ ተግባራትን ያከናውናሉ። ተመሳሳይ ቅዱስ መጽሐፍን ይከተላሉ። እንዲሁም ተመሳሳይ እምነቶችን ይከተላሉ።

አላህ—ለሁሉም ፍጡራን እውነተኛው ብቸኛ አምላክ የሚል የዐረብኛ ቃል ነው—ሁሉም ሰብዓዊ ፍጡራን ላይ በፍትህና በእኩልነት ይፈርዳል። አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ በብዙ አንቀጾች ላይ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ፍትሃዊ አያያዝ እና ምንዳ አፅንዖት ሰጥቷል።

**የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “አላህ ምእመናንንና ምእምናትን ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ በመኖሪያ ገነቶችም ውስጥ መልካም መኖሪያ ቤቶችን ቃል ገብቶላቸዋል።”**

ቁርኣን 9:72

**አሸናፊውና የላቀው እንዲህ ብሏል፦ “ከእናንተ ከወንድ ወይም ከሴት የሠሪን ሥራ አላጠፋም። ከፊላችሁ ከከፊሉ ነው።”**

ቁርኣን 3:195

ምንዳ የሚሰጠው በሰውየው ተግባር እንጂ በፆታው እንዳልሆነ እነዚህ አንቀጾች ያስረዱናል። ፆታ አንድን ሰው በመሸለም ወይም በመፍረድ ረገድ ምንም ሚና አይጫወትም።

ኢስላምን ከሌሎች እምነቶች ጋር ስናነፃፅር ኢስላም በሁለቱ ፆታዎች መካከል ፍትህን ሲያሰፍን እንመለከታለን።

CONTENTS


























ለምሳሌ ያህል፣ ኢስላም ሐዋ ከተከለከለችዋ ዛፍ ስለበላች ከአደም የበለጠ ተጠያቂ ናት የሚለውን አስተሳሰብ አይቀበልም። ይልቁንም፣ እንደ ኢስላም አስተምህሮት አደም እና ሐዋ ሁለቱም ኃጢአት ሰርተዋል። አላህም ንስሐቸውን ተቀብሎ ይቅር ብሏቸዋል።

# የመማር መብት እኩልነት

ወንድም ሴትም እውቀትን እንዲያገኙ እኩል ተበረታተዋል። ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ “እውቀትን መፈለግ በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው።”

በተጨማሪም፣ በነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ዘመን ሙስሊም ሴት ምሁራን ነበሩ። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ከቤተሰባቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከባልደረቦቻቸው ወይም ከሴት ልጆቻቸው ነበሩ። ከእነዚህም ውስጥ ዋነኛዋ የነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ባለቤት የሆኑት ዓኢሻ ናቸው። በእርሳቸውም አማካኝነት የሸሪዐ እሩብ ያህሉ ተላልፏል።

ሌሎችም የፊቅህ (የእስልምና ህግ) ሊቃውንትና ምሁር ሴቶች ነበሩ። ታዋቂ ምሁራንም በእነርሱ እጅ ተምረዋል።

# የትዳር ጓደኛን የመምረጥ እኩል መብት

ኢስላም ሴትን አክብሯል። በዚህም የትዳር ጓደኛዋን የመምረጥ መብት ሰጥቷታል። በተጨማሪም ስታገባ የራሷን የቤተሰብ ስም እንድትይዝ አስችሏታል።

ይህ ሆኖ ሳለ፣ ብዙ ሰዎች ወላጆች ሴት ልጆቻቸውን ለጋብቻ ያስገድዳሉ የሚል ግምት አላቸው። ይህ ግን ባህላዊ ልማድ እንጂ በእስልምና ምንም መሠረት የለውም። እንዲያውም በሸሪዐ የተከለከለ ነው።

በነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ዘመን አንዲት ሴት ወደ እሳቸው መጣችና “አባቴ ዝቅ ያለ ማህበራዊ ደረጃውን ከፍ ለማድረግ አስቦ በማስገደድ ለአጎቴ ልጅ ዳረኝ።” አለች። ነቢዩም (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ወደ ልጅቷ አባት ልከው፣ ከቀረበ በኋላ ልጅቷ ትዳሯን እንድትቀጥል ወይም እንድትሸረው የመምረጥ መብት ሰጧት። እሷም እንዲህ አለች፦ “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አባቴ ያደረገውን ተቀብያለሁ። ነገር ግን ለሴቶች በጉዳዩ ላይ የወንዶች ብቻ ስልጣን እንደሌለ ማሳየት ፈልጌ ነው።"

# እኩል ናቸው ግን ይለያያሉ

ወንዶችና ሴቶች እንደ አጠቃላይ መርህ እኩል መብቶች ቢኖራቸውም፣ ለእያንዳንዳቸው የተሰጡት የተወሰኑ መብቶችና ኃላፊነቶች ግን ተመሳሳይ አይደሉም። ለወንዶችና ለሴቶች ያሉት መብቶችና ኃላፊነቶች ተመጋጋቢ እንጂ ተመሳሳይ አይደሉም።

ከውጫዊና ውስጣዊ የአካል ልዩነቶች በተጨማሪ ሳይንቲስቶች የወንዶችና የሴቶች አእምሮዎች ቋንቋን፣ መረጃንና ስሜትን በማስተናገድ ላይ ብዙ ልዩነቶች እንዳሉ ያውቃሉ። ለምሳሌ ያህል ብቻ ብንጠቅስ፦

CONTENTS






የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲው የሶሺዮ ባዮሎጂ ምሁር የሆኑት ኤድዋርድ ዊልሰን እንዲህ ይላሉ፦

"ሴቶች በቃል ክህሎቶች፣ በመተሳሰብ እና በማኅበራዊ ክህሎቶች ከወንዶች የተሻሉ ሲሆኑ፣ ወንዶች ደግሞ – ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ – ነጻነትን በመሻት፣ በመሪነት፣ በቦታ ግንዛቤ (spatial) እና በሂሳብ ክህሎቶች፣ እንዲሁም ከደረጃ ጋር በተያያዘ የጥቃት ባህሪ እና ሌሎች ባህሪያት የተሻሉ የመሆን ዝንባሌ አላቸው።"

ሁለቱን ፆታዎች በተመሳሳይ መንገድ ማስተናገድ እና በመካከላቸው ያሉትን ልዩነቶች ችላ ማለት ጥበብ የጎደለው እይታ ነው።

ኢስላም ወንዶችና ሴቶች ተመጋጋቢ ግን የተለያዩ ሚናዎች እንዳላቸው ያስተምራል። እነዚህ ሚናዎች ለተፈጥሯቸው ይበልጥ ተስማሚ ናቸውና።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

> “ወንድም እንደ ሴት አይደለም።” .
>
> ቁርኣን 3:36

> “የፈጠረ አምላክ እርሱ እውቀተ ረቂቁ፣ ውስጥ አዋቂው ሲሆን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?”
>
> ቁርኣን 19:36

# የቤተሰብ አባላት

አላህ ወንዶችንና ሴቶችን የፈጠረው ልዩ የሆኑ ሚናዎች፣ ክህሎቶችና ኃላፊነቶች እንዲኖራቸው አድርጎ ነው። እነዚህ ልዩነቶች የበላይነትን ወይም ዝቅተኝነትን የሚያመለክቱ ሳይሆኑ፣ ይልቁንም የልዩ ዘርፍ ባለቤትነትንና አንዱ ለሌላው አሚይነትን ያሳያሉ።

በኢስላም ቤተሰብ ማዕከላዊ ፋይዳ አለው። ወንድ የቤተሰቡን ቁሳዊ ብልጽግና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ሴት የአካላዊ፣ የትምህርታዊና የስሜታዊ ብልጽግና አስተዋጽኦ ታደርጋለች። ይህ ደግሞ ከመፎካከር ይልቅ መደጋገፍን ያበረታታል። ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን የጋራ ኃላፊነቶች ሲወጡ፣ ጠንካራ ቤተሰቦች ይገነባሉ። በዚህም የተነሳ የተሳሰሩ ማኅበረሰቦች ይፈጠራሉ።

ከስሜታዊ አቅጣጫ ደግሞ፣ ወንዶችና ሴቶች አንዳቸው በሌላቸው እንጂ ደስተኛ ሕይወት መኖር አይችሉም። አላህ እንዲህ ሲል መግለፁ ምንኛ ያማረ ነው፦

> “እነርሱ ለእናንተ ልብስ ናቸው። እናንተም ለእነርሱ ልብስ ናችሁ።”
>
> ቁርኣን 2:187

ልብስ ምቾትን፣ ሙቀትንና ደህንነትን ይሰጣል። በተጨማሪም ሰውን ያሳምራል፤ ጉድለቶችንም ይሸፍናል።

በትዳር ጓደኞች መካከል ያለው ግንኙነትም በዚሁ መንገድ ይታያል። እያንዳንዱ የትዳር ጓደኛ ለሌላው መሸፈኛና መርጊያ ነው።

CONTENTS




# በትዳር ግንኙነቶች ውስጥ መዋደድና እዝነት

ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ባሎች ሚስቶቻቸውን በመልካም ሁኔታ እንዲይዙ እንዲህ ሲሉ አበረታተዋል፦

“ከእናንተ በላጫችሁ ለቤተሰቡ በላጭ የሆነው ነው።” (ቲርሚዚይ ዘግበውታል - 3895)

> የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አሉ።”
>
> ቁርኣን 30:21

የነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ባለቤት የሆኑት ዓኢሻ በቤታቸው ውስጥ ስላለው የነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) ስነምግባር ተጠይቀው እንዲህ ብለዋል፦ "ከእናንተ አንዱ በቤቱ ውስጥ እንደሚሆነው ነበሩ። ነገር ግን እርሳቸው ይበልጥ ገርና ቸር ነበሩ። ሚስቶቻቸውን በመደበኛ የቤት ውስጥ ሥራዎች ለመርዳትም ዝግጁ ነበሩ። ልብሳቸውን ይሰፉ፣ ጫማቸውንም ያበጁ ነበር።” በአጠቃላይ ሚስቶቻቸው በሚያደርጉት በማንኛውም ሥራ ይረዱ ነበር።

# ለእናትና ለሴት ልጆች ያለው ከፍ ያለ ደረጃ

እናት በተለይ በመጀመሪያዎቹ የልጅነት ዓመታት በርህራሄዋ፣ በልዩ እንክብካቤዋ እና በፍቅሯ በልጇ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ታሳድራለች። የማኅበረሰብ ስኬት የሚመነጨው ከእናቶች እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። ስለዚህ፣ ኢስላም እናቶችን የሚያከብርና ደረጃቸውን ከፍ የሚያደርግ መሆኑ ትክክል ነው።

የላቀው አላህ በክቡር ቁርኣኑ እንዲህ ብሏል፦

> “ሰውንም በወላጆቹ በጎ መዋልን በጥብቅ አዘዝነው። እናቱ በችግር ላይ ሆና አረገዘችው። በችግርም ወለደችው።” ቁርኣን
>
> ቁርኣን 46:15

ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) አንድ ጊዜ እንዲህ ተብለው ተጠየቁ፦ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ከሰዎች ሁሉ መልካም አያያዜ ይበልጥ የሚገባው ማን ነው?" እሳቸውም "እናትህ!" አሉ። ሰውየውም ሁለት ጊዜ "ከዚያስ ማን ነው?" ብሎ ጠየቀ፤ እሳቸውም ያንኑ መልስ ሰጡ። በአራተኛው ጊዜ ብቻ ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) "ከዚያ አባትህ" አሉ። ቡኻሪ (5971) እና ሙስሊም (2548) ዘግበውታል።

መልካም ምንዳ የሚሰሰጠው እናቶችን በጥሩ ሁኔታ በመያዝ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ኢስላም ሴት ልጆችን በማሳደግ ላይ በተጨባጭ ልዩ ምንዳ መድቧል። ይህ ምንዳ ደግሞ ወንድ ልጆችን በማሳደግ ላይ እንኳ ያልተሰጠ ነው።

ነቢዩ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ አሉ፦ “ሶስት ሴት ልጆች ያሉትና የሚያኖራቸው፣ የሚራራላቸውና የሚንከባከባቸው ሰው፣ ጀነት በእርግጥ ግዴታ ትሆንለታለች።” “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ሁለት ቢሆኑስ?” ተባለ። እሳቸውም “ሁለት ቢሆኑም (ጀነት ግዴታ ትሆንለታለች)” አሉ። የሆኑ ሰዎች “ አንድ ብትሆንስ?' ተብለው ቢጠየቁ ኖሮ፦ 'አንድ ብትሆንም!' ይሉ ነበር" አሉ። (አሕመድ ዘግበውታል - 14247)

CONTENTS






# መደምደሚያ

ከእስልምና በፊት ሴት እንደነውር ትታይ ነበር። ታዳጊ ሴት ልጆች ከነሕይወታቸው ይቀበሩ ነበር። ዝሙት ተስፋፍቶ ነበር። ፍቺ በባሎች እጅ ብቻ ነበር። ውርስም ለባለሥልጣኖች ብቻ ነበር። ጭቆናና በደልም ነገሠ። ከዚያም ኢስላም መጣና እነዚህን ልማዶች አስቀርቶ ለሴት ክብሯንና መብቷን መለሰላት።

አሁንም ቢሆን "በበለጸጉ አገሮች" ሴቶች ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ ማግኘት ይቅርና አክብሮት፣ ክብርና ሞገስ አይሰጣቸውም። ኢስላም ግን ሴቶችን የከበሩና ውድ አድርጎ ይመለከታቸዋል። ሊናቁ ወይም ሊዋረዱ አይገባም። በአንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ወይም ሙስሊም ቤተሰቦች ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርሰው በደል አንዳንዶች በተሳሳተ መንገድ በሚከተሏቸው ባሕላዊ ምክንያቶች የተነሳ ነው እንጂ በእስልምና ምክንያት አይደለም። ኢስላም አፋኝ ሃይማኖት ከሆነ ታዲያ ለምንድን ነው በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ሴቶች በፈቃደኝነት ኢስላምን የሚቀበሉት?

በመጨረሻም፣ የወንዶችና የሴቶች ፈጣሪና ሲሳይ ሰጭ በሆነው በጌታችን ቃል እንቋጫለን።

**“ሙስሊሞች ወንዶችና ሙስሊሞች ሴቶች፣ ምእምናንና ምእምናትም፣ ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶችም፣ እውነተኞች ወንዶችና እውነተኞች ሴቶችም፣ ታጋሾች ወንዶችና ታጋሾች ሴቶችም፣ አላህን ፈሪዎች ወንዶችና አላህን ፈሪዎች ሴቶችም፣ መጽዋቾች ወንዶችና መጽዋቾች ሴቶችም፣ ጿሚዎች ወንዶችና ጿሚዎች ሴቶችም፣ (ካልተፈቀደ ሥራ) ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች ወንዶችና ጠባቂ ሴቶችም፣ አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም፣ አላህ ለእነርሱ ምሕረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል።።።”**

ቁርኣን 33:35

CONTENTS



- ስለ ኢስላም አጭር ትውውቅ
- ነብዩ ሙሐመድ
- መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው
- የአምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም
- ቁርኣን
- የህይወት አላማ ምንድን ነው?
- ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች
- የሴቶች መብቶች በኢስላም
- የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር
- ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም


# የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር

AMHARIC (09/10) العلوم في الإسلام FREE COPY

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ “እርሱም (ቁርኣን) እውነት መሆኑ ለእነርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን።”

ቁርኣን 41:53




جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES


Your Path To Peace..

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
www.islamicic.com

دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

تصريح رقم:
(2017/139)

CONTENTS

























ቁርኣን - የእስልምና ቅዱስ መጽሐፍ - ከአላህ ወደ ሰው ልጆች የተላከ የመጨረሻው ራዕይ (ወሕይ) ነው። እንዲሁም ለነቢያት ከወረደው የራዕይ ሰንሰለት ውስጥ መቋጫው ነው።

ምንም እንኳን ቅዱስ ቁርኣን (ከ1400 ዓመታት በፊት የወረደ ከመሆኑ ጋር) በዋነኛነት የሳይንስ መጽሐፍ ባይሆንም፣ ነገር ግን ለቴክኖሎጂና የሳይንስ ዕውቀት መሻሻል ምስጋና ይግባውና በቅርቡ የተገኙ ሳይንሳዊ እውነታዎችን የሚያመለክቱ ፍንጮችን ይዟል።

እስልምና ማሰላሰልንና ሳይንሳዊ ምርምርን ያበረታታል። ምክንያቱም የፍጥረትን ተፈጥሮ መረዳት ሰዎች የፈጣሪያቸውን ታላቅነት የበለጠ እንዲያደንቁ እና የእርሱን ኃይልና ጥበብ እንዲረረዱ ያስችላቸዋል።

ቁርኣን፡ ሳይንስ ገና ያልዳበረ በሆነበት ዘመን ነው የወረደው። በዚያን ጊዜ ቴሌስኮፖች፣ ማይክሮስኮፖች ወይም ከዛሬው ቴክኖሎጂ ጋር የሚቀራረብ ምንም ነገር አልነበረም።

ሰዎች ፀሐይ በምድር ዙሪያ እንደምትዞር እና ሰማይ በጠፍጣፋው ምድር ማዕዘናት ላይ በአምዶች እንደተንጠለጠለ ያምኑ ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ፣ ቁርኣን ወረደ። ይህም ከሥነ ፈለክ እስከ ስነ ህይወት፣ ከስነ ምድር እስከ ሥነ እንስሳት ድረስ ባሉ ጉዳዮች ዙሪያ በርካታ ሳይንሳዊ እውነታዎችን የሚያመላክቱ ግልጽ ፍንጮችን ይዟል።

ቁርኣን ውስጥ ከሚገኙ በርካታ ሳይንሳዊ እውነታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

“ሕያው የሆነንም ነገር ሁሉ ከውሃ ፈጠርን። አያምኑምን?”.

ቁርኣን 21:30

## 1 የሕይወት አመጣጥ

ውሃ የሁሉም የሕይወት ዓይነቶች መነሻ እንደሆነ ይጠቀሳል። ሁሉም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከሕዋሳት የተሠሩ ናቸው። አሁን ደግሞ ሕዋሳት በአብዛኛው ከውሃ የተሠሩ መሆናቸውን እናውቃለን።

ይህ እውነታ የተገኘው ማይክሮስኮፕ ከተፈለሰፈ በኋላ ነው። በዓረብ ባሕረ ገብ መሬት (pensula) በረሃዎች ውስጥ፣ በምድር ላይ ያሉ የሕይወት ዓይነቶች በሙሉ ከውሃ የመጡ ናቸው ብሎ ማንም ያሰበዋል ተብሎ የሚገመት አልነበረም።

## 2 የሰው ልጅ ፅንስ እድገት


አላህ ስለ ሰው ልጅ ፅንስ እድገት ደረጃዎች እንዲህ ይናገራል፦

“በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው። ከዚያም ጠብታዋን የረጋ ደም (ዐለቃህ) አድርገን ፈጠርን። የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ (ሙድጋህ) አድርገን ፈጠርን።...”

ቁርኣን 23:12-14

- “ዐለቃህ" የሚለው ቃል ሦስት ትርጉሞች አሉት፦ ጥገኛ (parasite)፣ የተንጠለጠለ ነገር (suspended thing) እና የደም መርጋት (blood clot)።
- "ሙድጋህ" (مُضْغَة) ደግሞ የታኘከ ነገር ማለት ነው። የፅንስ ተመራማሪዎች እነዚህ ቃላት የፅንስ አፈጣጠርን ለመግለጽ መዋላቸው ትክክለኛ መሆኑንና ከአሁኑ ሳይንሳዊ የእድገት ደረጃዎች ግንዛቤያችን ጋር የሚጣጣም መሆኑን አስተውለዋል።

CONTENTS


































እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የሰው ልጅ ፅንስ እድገት ደረጃዎች አደረጃጀትና ምድብ ብዙም የታወቀ አልነበረም። ይህ ማለት በቁርኣን ውስጥ ያሉት የሰው ልጅ ፅንስ ገለጻዎች በ7ኛው ክፍለ ዘመን ከነበረው ሳይንሳዊ ዕውቀት ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ አይችሉም።

## 3 የዩኒቨርስ መስፋፋት

የሥነ ፈለክ ጥናት ያልዳበረ በነበረበት ጊዜ፣ የሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ ወረደ፦

**“ሰማይንም በኃይል ገነባናት። እኛም በእርግጥ አስፊዎች ነን።”**

ቁርኣን 51:47

በአንቀጹ ውስጥ ከተፈለጉት ትርጉሞች አንዱ አላህ ዩኒቨርሱን (ማለትም ሰማይን) እያሰፋ መሆኑን ነው። ሌሎች ትርጉሞች ደግሞ፡ አላህ ዩኒቨርሱን ይጠብቃል።በእርሱ ላይም ስልጣን አለው የሚሉትን ያካትታሉ።

ዩኒቨርስ እየሰፋ መሆኑ (ለምሳሌ፡ ፕላኔቶች እርስ በርሳቸው እየተራራቁ መሆኑ) የተገኘው ባለፈው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነው። የፊዚክስ ሊቅ ስቴፈን ሃውኪንግ "የጊዜ አጭር ታሪክ" በተሰኘው መጽሐፉ ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦

"ዩኒቨርሱ እየሰፋ መሆኑ መታወቁ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ታላላቅ የአስተሳሰብ አብዮቶች ውስጥ አንዱ ነበር።"

ቁርኣን ቴሌስኮፕ ከመፈጠሩ በፊት የዩኒቨርስን መስፋፋት ይጠቁማል!

## 4 የብረት መውረድ

ብረት በምድር ላይ በተፈጥሮ የሚገኝ ንጥረ ነገር አይደለም። ይልቁንም ከውጪ ጠፈር የመጣ ነው። ሳይንቲስቶች እንዳረጋገጡት፣ ከቢሊዮን ዓመታት በፊት ምድር ከሩቅ ኮከቦች ፍንዳታ የመጣ ብረትን በያዙ ሜትሮራይቶች ተመታለች።

“ብረትንም በውስጡ ብርቱ ሃይልና ለሰዎችም መጠቀሚያዎች ያሉበት ሲሆን አወረድን።”

ቁርኣን 57:25

አላህ በአንቀጹ ውስጥ “አወረድን” የሚለውን ቃል ተጠቅሟል።

ብረት ወደ ምድር የወረደው በሜትሮራይቶች አማካኝነት ነው የሚል ጠንካራ ሳይንሳዊ እይታ አለ። ይህ ደግሞ የ7ኛው ክፍለ ዘመን ያልዳበረ ሳይንስ ሊያውቀው የማይችል ነገር ነበር።

## 5 የሰማይ ጥበቃ

ሰማይ፣ ምድርንና ነዋሪዎቿን ከፀሐይ ገዳይ ጨረሮች እንዲሁም ከህዋው ከባድ ቅዝቃዜ በመጠበቅ ረገድ ትልቅ ሚና ትጫወታለች።


አላህ (ክብርና ልቅና ለሱ ይሁን) በሚቀጥለው አንቀጽ ሰማይን እንድንመለከት ይጋብዘናል፦

“ሰማይንም የተጠበቀ ጣራ አደረግን። እነርሱም ከተዓምራቶቿ ዘንጊዎች ናቸው።”

[ቁርኣን 21:32

ቁርኣን የሰማይን ጥበቃ እንደ አንዱ የአላህ ችሎታ ምልክቶች አድርጎ ይጠቅሳል። ይሁን እንጂ የመከላከያ ባህሪያቶቿ የተገኙት በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተደረገው ሳይንሳዊ ምርምር ነው።

CONTENTS



































## 6 ተራራዎች

አላህ ትኩረታችንን ወደ ተራሮች ዋና ባህሪ ይስባል፦

ቁርኣን የተራሮችን ጥልቅ ስሮች (መሠረቶች) "ችንካሮች" በሚለው ቃል በትክክል ይገልፃል።

ለምሳሌ፣ የኤቨረሰት ተራራ ግምታዊ ከፍታ ከምድር ገጽ 9 ኪሎሜትር አካባቢ ሲሆን፣ ሥሮቹ ግን ከ125 ኪሎሜትር በላይ ጥልቀት አላቸው።

> “ምድርን ምንጣፍ አላደረግንምን? ጋራዎችንም ችካሎች አላደረግንምን?”
>
> ቁርኣን 78:6-7




ተራሮች ጥልቅ የሆኑ፣ "ችንካር" የመሰሉ ስሮች እንዳሏቸው የታወቀው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የፕሌት ቴክቶኒክስ ንድፈ ሐሳብ (theory of plate tectonics) ከዳበረ በኋላ ነው። የላቀው አላህ በክቡር ቁርኣን ላይ እንዲህ ሲል ጠቁሟል፦ "በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለባት።" (ቁርኣን 16:15)

ይህ ደግሞ በሳይንሳዊ መንገድ መረዳት ላይ የተደረሰው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ነው።

## 7 የፀሐይ ምህዋር

በ1512 የሰነ ፈለክ ተመራማሪው ኒኮላስ ኮፐርኒከስ ፀሐይ በፀሐይ ሥርዓት መሃል ላይ ቋሚ (የረጋች) እንደሆነች እና ፕላኔቶች በዙሪያዋ እንደሚሽከረከሩ የሚገልጽ ንድፈ ሐሳብ አቀረበ። ይህ እምነት በሰነ ፈለክ ተመራማሪዎች ዘንድ እሰከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ተሰፋፍቶ ነበር።


አሁን ግን ፀሐይ ቋሚ አለመሆኗ፣ ይልቁንም በሚልኪ ዌይ ጋላክሲያችን ማዕከል ዙሪያ በምህዋር እንደምትጓዝ የተረጋገጠ እውነታ ነው።

> “እርሱም ሌሊትንና ቀንን፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የፈጠረ ነው። ሁሉም በፈለካቸው ውስጥ ይዋኛሉ።”
>
> ቁርኣን 21:33

## 8 በውቅያኖስ ውስጥ ያሉ የውስጥ ማዕበሎች

ማዕበሎች የሚከሰቱት በውቅያኖስ ወለል ላይ ብቻ እንደሆነ በተለምዶ ይታሰብ ነበር። ይሁን እንጂ የውቅያኖስ ተመራማሪዎች ከባህር ገጽ በታች የሚከሰቱ የውስጥ ማዕበሎች መኖራቸውን ደርሰውበታል። እነዚህ ማዕበሎች በሰው ዓይን የማይታዩ ሲሆኑ፣ ሊታወቁ የሚችሉት በልዩ መሣሪያዎች ብቻ ነው።

CONTENTS
































## ቁርኣን እንዲህ ሲል ይገልጻል፦

“ከበላዩ ማዕበል በዚያ ላይ ደመና ያለበት ማዕበል የሚሸፍነው ጥልቅ የባህር ጨለማ። ከፊላቸው ከከፊሉ በላይ የሆኑ ጨለማዎች ናቸው።”

ቁርኣን 24:40

ይህ መግለጫ አስደናቂ ነው። ምክንያቱም ከ1400 ዓመታት በፊት በጥልቅ ውቅያኖሶች ውስጥ የውስጥ ማዕበሎችን ለመለየት የሚያስችል ልዩ መሣሪያ አልነበረምና።

## 9 ውሸት እና እንቅስቃሴ

በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን አንድ ጨካኝና ወሰን አላፊ የጎሳ መሪ ይኖር ነበር። አላህም እሱን ለማስጠንቀቅ አንድ አንቀጽ አወረደ፦

“ይተው! ባይከለከል እናቱን ይዘን እንጎትተዋለን።ውሸታም አጥፊ የሆነችዋን እናቱን።”

ቁርኣን 96:15-16

አላህ ይህን ሰውዬ በቀጥታ "ውሸታም" ብሎ ብቻ አልገለጸውም። ይልቁንም ግምባሩን (የአንጎልን የፊት ክፍል) "ውሸታም" እና "ኃጢአተኛ" ብሎ የገለጸው ሲሆን፣ እንዲቆምም አስጠንቅቆታል።

በርካታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአንጎል የፊት ክፍል (frontal lobe) ለሁለቱም ማለትም ለውሸት እና ፈቃደኛ እንቅስቃሴ (voluntary movement) ተጠያቂ ነው። በዚህም ምክንያት ለኃጢአትም ተጠያቂ ይሆናል።

እነዚህ ተግባራት የተገኙት በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተገነቡ የሕክምና ምስል መሣሪያዎች ነው።


## 10 የማይቀላቀሉ ሁለት ባሕሮች

ፈጣሪያችን ስለ ባሕሮች እንዲህ ይላል፦

“ሁለቱን ባሕሮች የሚገናኙ ሲሆኑ ለቀቃቸው። (እንዳይዋሐዱ) በመካከላቸው ጋራጅ አለ።”

ቁርኣን 55:19-20

"የገጽታ ውጥረት" (Surface Tension) ተብሎ የሚጠራ አንድ ፊዚካዊ ኃይል በአቅራቢያ ያሉ የባህር ውሃዎች በየራሳቸው የጥግግት (density) ልዩነት ምክንያት እንዳይቀላቀሉ ይከላከላል። ይህም በመካከላቸው ቀጭን ግድግዳ እንዳለ ያህል ነው። የውቅያኖስ ተመራማሪዎች ይህን ክስተት ያገኙት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ነው።




## ነቢዩ ሙሐመድ ቁርኣንን ሊያዘጋጁ ይችሉ ነበር?

ነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) በታሪክ ኡምሚይ (illiterate) በመሆናቸው ይታወቃሉ። ማለትም ማንበብም ሆነ

CONTENTS





መጻፍ አይችሉም ነበር። እንዲሁም በቁርኣን ውስጥ ያለውን ሳይንሳዊ ትክክለኛነት ሊያስረዳ በሚችል በምንም ዓይነት መስክ አልተማሩም።

አንዳንዶች ቁርኣንን በዘመኑ ከነበሩ ምሁራን ወይም ሳይንቲስቶች ገልብጧል ብለው ሊናገሩ ይችላሉ። ነገር ግን እንደዚያ ቢሆን ኖሮ፣ በቁርኣን ውስጥ በዚያን ጊዜ የተለመዱ የነበሩ የተሳሳቱ ሳይንሳዊ ግምቶችን ባገኘን ነበር። ሆኖም፣ ቁርኣን ምንም ስህተቶችን አልያዘም -ሳይንሳዊም ሆነ ሌሎች ስህተቶችን።

ቁርኣን አዳዲስ ሳይንሳዊ እውነታዎች ሲገኙ ተቀይሯል የሚለው የአንዳንዶች ክስም ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ቁርኣን በመጀመሪያው በዐረብኛ ቋንቋው ተጠብቆ የቆየ ነውና። ይህ ደግሞ በታሪክ የተመዘገበ እውነታ ነው። ይህ በራሱ አንድ ተአምር ነው።

## እንዲሁ የአጋጣሚ ነገር ይሆን?

ይህ በራሪ ወረቀት ሊሆኑ የሚችሉትን ሳይንሳዊ ተአምራትን ብቻ የሚያተኩር ቢሆንም፣ በቅዱስ ቁርኣን ውስጥ የተጠቀሱ ብዙ አይነት የተረጋገጡ ተአምራት አሉ። ለምሳሌ፦ ታሪካዊ ተአምራት፣ የተፈጸሙ ትንቢቶች፣ ልዩ የቋንቋ እና ስነ-ጽሑፋዊ አቀራረቦች (styles)፣ እነዚህ አቀራረቦች በአድማጩ ላይ ያላቸው ጥልቅ ተጽዕኖ፣... እነዚህ ሁሉ ተአምራት ዝም ብለው የአጋጣሚ ነገሮች ሊሆኑ አይችሉም። ይልቁንም፣ ክቡር ቁርኣን የሁሉም ሳይንሳዊ ህግጋት ፈጣሪ ከሆነው አላህ ዘንድ የመጣ መሆኑን የሚያሳዩ ግልጽ ማስረጃዎች ናቸው።

እርሱ አንድ አምላክ ሲሆን፣ ሁሉንም ነቢያት በአንድ መልእክት የላከ ነው። ይህም አንድን አላህ ብቻ ማምለክ እና የመልክተኞቹን ትምህርቶች መከተል ነው።

ቁርኣን የሰው ልጆችን ያለ ዓላማ ይኖሩ ዘንድ አላህ እንዳልፈጠራቸው የሚያብራራ የመመሪያ መጽሐፍ ነው። ይልቁንም፣ በሕይወታችን ውስጥ ትልቅና ትርጉም ያለው ዓላማ እንዳለን ያስተምረናል። እሱም፦ የአላህን ፍጹምነት፣ ታላቅነት፣ ብቸኝነት ማወቅና እርሱን መታዘዝ ነው።

እያንዳንዱ ሰው በአላህ የተሰጠውን አእምሮውንና የማመዛዘን ችሎታውን የአላህን ተአምራት ለማሰላሰልና ለመገንዘብ መጠቀም የራሱ ድርሻ ነው። ቁርኣን ደግሞ እጅግ በጣም ዋናው ተአምር ነው።

> “እርሱም (ቁርኣን) እውነት መሆኑ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን።”
>
> ቁርኣን 41:53

**ቁርኣንን እንብብና ውበቱን እንዲሁም እውነቱን እወቅ። በዚህም ስኬትን ታገኛለህና!**

HOTLINE
+971 56 204 2045
islamicicdxb
islamicic.com  info@islamicic.com  +971 4 355 5223
DOWNLOAD AMHARIC FLYERS
www.iicdxb.com/amharic

CONTENTS


ስለ እስላም አጭር ትውውቅ

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በነሱም ላይ ይሁን)

መሲሑ የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ናቸው

የእምላክ ጽንሰ-ሐሳብ በኢስላም

ቁርኣን ለሙላው የሰው ዘር የመጨረሻው ራዕይ

የህይወት አላማ ምንድን ነው?

ስለ ኢስላም የተዛቡ ግንዛቤዎች

የሴቶች መብቶች በኢስላም

የቁርኣን ሳይንሳዊ ተአምር

ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም


# ሞት እና የመጨረሻው ዓለም በኢስላም

AMHARIC (10/10) الموت والآخرة في الإسلام FREE COPY

"ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት። ከዚያም ወደኛ ትመለሳላችሁ።"

ቁርኣን 29:57


جمعية دار البر
Dar Al Ber Society
www.daralber.ae

الإمارات
THE EMIRATES

Your Path To Peace..


مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
التعريف بالإسلام

www.islamicic.com

تصريح رقم:
(2017/139)

دائرة الشؤون الإسلامية والعمل الخيري
Islamic Affairs & Charitable Activities Department

CONTENTS


























# ሞት ቅርብ ነው።

ሞት መሸሽ የማንችለው፣ በየቀኑ፣ በየሰዓቱ እልፎ ተርፎም በየደቂቃው እየቀረበ የሚመጣ እውነት ነው። እንደ ሲአይኤ (CIA) የ2007 "ዘ ወርልድ ፋክትቡክ" መጽሐፍ ከሆነ፣ በየሰኮንዱ ሁለት ሰዎች ያህል ይሞታሉ። ይህም በዓመት ወደ 57.9 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ይሞታሉ ማለት ነው። ማንኛውም ሰው፣ ዕድሜው፣ ጤንነቱ፣ አስተዳደጉ፣ ማኅበራዊ ደረጃው ወይም ሃይማኖተኝነቱ ምንም ይሁን ምን ይህን የማይቀር እጣ ፈንታ ይጋፈጣል።

"የትም ስፍራ ብትሆኑ በጠነከሩ ሕንጻዎች ውስጥ ብትሆኑም እንኳ ሞት ያገኛችኋል።"

ቁርኣን 4:78

ታዲያ ያለፉት ነገሥታት፣ ቢሊየነሮች እና ኃያላን ሰዎች የት አሉ?

የውበት፣ የዝና እና የነጠሩ ሃሳቦች ባለቤቶችስ የት አሉ?

# የሞት እውነታ

አላህ በቁርኣን እንደነገረን እኛን የፈጠረን እርሱን ብቻ እንድናመልከው ነው። ይህንንም ህይወት ያንን ታላቅ ዓላማ በትክክል የሚያሟላ ማን እንደሆነ ለማወቅ ፈተና አድርጎታል።

አላህ በቁርኣን እንደነገረን እኛን የፈጠረን እርሱን ብቻ እንድናመልከው ነው። ይህንንም ህይወት ያንን ታላቅ ዓላማ በትክክል የሚያሟላ ማን እንደሆነ ለማወቅ ፈተና አድርጎታል።

“ጋኔንንም ሰውንም እኔን ሊግገዙኝ እንጂ አልፈጠርኳቸውም።"

ቁርኣን 51:56


አላህ (ክብርና ልቅና ይግባው) የሞትንና የህይወትን አፈጣጠር ዓላማ እንዲህ ሲል ነግሮናል፦

"ያ የትኛችሁ ስራው ይበልጥ ያማረ እንደሆነ ሊሞክራችሁ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው።"

ቁርኣን 67:2


አንድ ሰው ለሞት የሚዘጋጀው የቀብር ሥነ ሥርዓት ወጪዎችን አስቀድሞ በመክፈል ወይም የሬሳ ሳጥን በመምረጥ ሳይሆን፣ የሕይወትን እውነተኛ ዓላማ በማሳካት ነው። ይህም አላህን ብቻ መገዛት፣ በትእዛዙ መሠረት መኖር እና መልካም ሥራዎችን መሥራት ነው። በእስልምና ውስጥ የአምልኮ ጽንሰ-ሐሳብ የሕይወትን እያንዳንዱን ገጽታ የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በጸሎት ብቻ የተገደበ አይደለም። አላህን የሚያስደስት ማንኛውም ተግባር የአምልኮ ዓይነት ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን፣ በዱንያም ሆነ በአኺራ ምንዳ አለው።


CONTENTS











# የሞት ቅጽበት

> "እያንዳንዷ ነፍስ ለነገ ምን እንዳስቀደመች ትመልከት።"
>
> ቁርኣን 59:18

በየቀኑ ብዙ የሞት ምሳሌዎችን እናያለን። ህመም ወይም ብጥብጥ የሌለበት ሞት ሰላማዊ ነው ብለን እናስባለን። ሆኖም ግን ይህ ሁልጊዜ እንደዚያ ይሆናል ማለት አይደለም።

አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱ ከአካሉ ትወጣለች። የሥጋው ውጫዊ ገጽታ የነፍስን ሁኔታ ላያንጸባርቅ ይችላል።

የነፍስ መረጋጋት ወይም መርረበሽ በሰውዬው ህይወት ውስጥ በተከናወነው ነገር ቀጥተኛ ውጤት ይሆናል። የሞቱ ቀጥተኛ ምክንያት ላይሆን ይችላል።

አስቀድመው ወደማያውቁት መዳረሻ የአንድ መንገድ ትኬት የያዙ ሁለት ሰዎችን እንደ ምሳሌ እንውሰድ። የመጀመሪያው ሰው የመድረሻውን ቋንቋ፣ ባህልና ልማዶች ለመማር ጊዜ ይወስዳል። ትክክለኛውን ገንዘብና ክትባቶችን ያገኛል። እናም የጉዞው ጊዜ ሲደርስ ምንም አይነት ድንገተኛ ነገር ሳይገጥመው ይደርሳል። በጥሩ ሁኔታ ስለተዘጋጀ ደህንነቱ የተጠበቀና ደስተኛ ነው።

በተቃራኒው፣ ሁለተኛው ሰው ለመዘጋጀት ቸልተኛ ሲሆን፣ ለመሄድ የጉዞው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ያለውን ቅጽበት ብቻ ይኖራል። ባልታወቀው መዳረሻው ላይ በፍርሃትና በግራ መጋባት ይደርሳል። አለመዘጋጀቱ አስከፊ ዕጣ ፈንታ እንዲገጥመው ያደርጋል። ምክንያቱም ይዞት የመጣው ሁሉ ምንም ፋይዳ የለውምና።

አላህ በቁርኣን እንዲህ ያለውን ቸልተኛ ሰው ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፦

**“ሞት ከእነርሱ ለአንዳቸው በመጣበት ጊዜ፦ ‘ጌታዬ ሆይ! ወደ ተውኩት (ዓለም) መልሱኝ። በተውኩት ነገር መልካምን ስራ ልሰራ እከጅላለሁና’ ይላል።”.**

ቁርኣን 23:99-100


በቁርኣን እንደምናየው የገሃነም እሳት ሰዎች በሷ ውስጥ የመግባታቸውን ምክንያት ሲጠየቁ እንዲህ ይላሉ፦

**" ’ከሰጋጆች አልነበርንም’ ይላሉ። ‘ምስኪንንም የምናበላ አልነበርንም። ከዘባራቂዎችም ጋር እንዘባርቅ ነበርን። በፍርዱም ቀን እናስተባብል ነበር። እርግጠኛው (ሞት) እስከ መጣን ድረሰ።’ "**

ቁርኣን 74:43-47

ሁላችንም ከሞት ጋር ቀጠሮ አለን። ሁላችንም ወደማይታወቅ መዳረሻ እንጓዛለን። ራስህን ጠይቅ፦ ለእሱ ተዘጋጅተሃል?

CONTENTS

































# የሕይወት ዓላማ

ሕይወት በሞት የሚጠናቀቅ ፈተና ነው። ነገር ግን የሰው ልጅ የሕልውናው ፍጻሜ አይደለም። ሞት ሲደርስ መልካም ሥራ የመሥራት ዕድሉ ይቋረጣል። ምህረትን መጠየቅም በጣም የዘገየ (ያለፈበት) ይሆናል። የሰው ልጅ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዚህ አጭር ሕይወት ውስጥ ባከናወናቸው እምነቶችና ሥራዎች ላይ ነው።

"የፈጠርናችሁ ለከንቱ መሆኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መሆናችሁን አሰባችሁን?"

ቁርኣን 23:115

የሰው ልጅ ሕይወት በሁለት ይከፈላል፦ በዚህ ዓለም ውስጥ አጭር ቆይታ እና በመጨረሻው ዓለም ዘላለማዊ ሕይወት። ጤነኛ አእምሮ ላለው ሰው፣ በመጨረሻው ዓለም ያለው ዘላለማዊ ደስታ በምድር ላይ ካለው ጠፊ ደስታ እጅግ የላቀና ዘላቂ እንደሆነ ግልጽ ነው።

አላህ ሰውን ፈጠረ። ነጻ ምርጫና ልክና ስህተትን መለያ አእምሮም ሰጠው። ይህም ለድርጊቶቹ ተጠያቂ ያደርገዋል።

መልካም ሰሪዎች የሚመነዱበትና በደለኞች የሚቀጡበት ሌላ ሕይወት ባይኖር ኖሮ፣ ያ ፍጹም ከሆነው የአላህ ፍትህ ጋር ይቃረን ነበር።

ስለዚህ፣ ሁሉም ነፍስ ለሰራችው ነገር የምትጠየቅበት የፍርዱ ቀን መኖር ከፍትህ መሰፈርቶች አንዱ ነው።

"ሙስሊሞችን እንደ ወንጀለኞች እናደርጋለንን? ምን ነካችሁ? እንዴት ትፈርዳላችሁ?!"

ቁርኣን 68:35-36

# የትንሣኤ ቀን

የሁሉም ሰው ተግባራት በዚህ ህይወት ውስጥ በትክክል ተመዝግበው ይቀመጣሉ። የላቀው አላህ እንዲህ ሲል እንደተናገረው፦

"(ለሰው ሁሉ) መጽሐፉም ይቀርባል። ወዲያውም አጥፊዎችን በውስጡ ካለው ነገር ፈሪዎች ሆነው ታያቸዋለህ። ‘ዋ ጥፋታችን! ለዚህ መጽሐፍ (ከሥራ) ትንሸንም ትልቅንም የቆጠራት ቢሆን እንጂ የማይተወው ምን አለው!’ ይላሉም። የሰሩትንም ነገር ሁሉ ቀራቢ ሆኖ ያገኙታል። ጌታህም አንድንም አይበድልም።"

ቁርኣን 18:49

"በላቸው፦ ‘ያ ከእርሱ የምትሸሹት ሞት እርሱ በእርግጥ አግኛችሁ ነው። ከዚያም ሩቁንና ቅርቡን ዓዋቂ ወደ ሆነው ጌታ ትመለሳላችሁ። ትሠሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል።"

ቁርኣን 62:8

CONTENTS






ያኔ ሁላችንም ተግባሮቻችንን በያዘው በዚያ መዝገብ ትክክለኛነት እንደመማለን። ከረጅም ጊዜ በፊት የረሳናቸውን ነገሮችም ያስታውሰናል። አላህ (ጥራትና ልቅና ለሱ ይሁን) እንዲህ ሲል እንደተናገረው፦

"አላህም (ያንን ሁሉ) ዘግቦታል። እነርሱም ረስተውታል።"

ቁርኣን 58:6

ይህን እውነት በጥልቀት ማሰላሰል፣ ማንኛውንም ኃጢአት ከመስራት እንድናፍር ሊያደርገን ይገባል። ምክንያቱም የምንሰራው ነገር ሁሉ ይመዘገብና በትንሳኤ ቀን በአላህ ፊት ይገለጣልና።

አላህ (ክብርና ልቅና ይገባውና) ሙታንን የማስነሳትና የመጠየቅ ችሎታው ላይ ለሚጠራጠሩ ሰዎች፣ የካሓዲያንን ጥያቄ እንዲህ ሲል ያወሳል፦

"አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲሆኑ ሕያው የሚያደርጋቸው ማነው?" ከዚያም በመልእክተኛው (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንደበት እንዲህ በማለት ይመልስላቸዋል፦ " 'ያ በመጀመሪያ ጊዜ የፈጠራት ሕያው ያደርጋታል። እርሱም በፍጥረት ሁሉ (ሁኔታ) ዐዋቂ ነው' በላቸው።"

ቁርኣን 36:78-79

# ገነትና ሲኦል

ገነት አምልኮት የሚገባው በሆነው አንድ አምላክ አላህ ለሚያምኑና መልካም ሥራ ለሚሠሩት ምንዳ ትሆናለች።

"የላቀው አላህ በክቡር ቁርኣኑ እንዲህ ብሏል፦ "የገነት ሰዎች ዛሬ በእርግጥ በሥራዎች ውስጥ ተደሳቾች ናቸው። እነርሱም ሚስቶቻቸውም በጥላዎች ውስጥ ናቸው። ባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ናቸው። በውስጧ ለእነርሱ ፍራፍሬዎች አሏቸው። ለእነርሱም የሚፈልጉት ሁሉ አልላቸው።"

ቁርኣን 36:55-57

ነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ውዳሴና ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል፦ "የከበረውና የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

**"ለደጋግ ባሮቼ ዓይን ያላየችውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ በሰው ልብ ላይ ያልታሰበውን ነገር አዘጋጅቻለሁ።"**

**ቡኻሪይ (4779) እና ሙስሊም (2824) ዘግበውታል።**

ከዚህ በተቃራኒ፣ በአላህ አንድነት የካዱና ያስተባበሉ ሰዎች እጣ ፈንታቸው እሳት ነው። እዚያም እንደዚህ ይባላሉ፦

"ይህቺ ያቺ ትቀጠሯት የነበረችው ገሀነም ናት። ትክዱ በነበራችሁት ምክንያት ዛሬ ግቧት (ይባላሉ)።"

ቁርኣን 36:63-64

CONTENTS






ለካሓዲዎችም ከባድ ቅጣት ይኖራቸዋል።

የላቀው አላህ እንዲህ ይላል፦ "ገሀነም መጠባበቂያ (ሰፍራ) ናት። ለሕግ ተላላፊዎች መመለሻ ስትሆን። በውስጧ ብዙን ዘመናት ነዋሪዎች ሲሆኑ፤ በውስጧ ቅዝቃዜንም መጠጥንም አይቀምሱም። ግን ሙቅ ውሃንና እዥን (ይቀምሳሉ)። ተስማሚን ምንዳ ይምመነዳሉ። እነርሱ ምርመራን የማይፈሩ ነበሩና። በአንቀጾቻችንም ማስተባበልን አስተባበሉና። ነገሩንም ሁሉ የተጻፈ ሲሆን አጠቃለልነው። ቅመሱም ቅጣትንም እንጅ (ሌላን) አንጨምራችሁም (ይባላሉ)።"

ቁርኣን 78:21-30

# መደምደሚያ

የላቀው አላህ እንዲህ ይላል፦ "አንተ ሰው ሆይ! በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ?! በዚያ በፈጠረህ፣ አካለ ሙሉም ባደረገህ ባስተካከለህም። በማንኛውም በሻው ቅርፅ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ?)። ተከልከሉ፤ በእውነቱ በፍርዱ ቀን ታስተባብላላችሁ።"

ቁርኣን 82:6-9

ሁላችንም ፈጥናም ይሁን ዘግይቶ የሞትን ጥሪ እንደምንቀበል ሁልጊዜ ማስታወስ አለብን። የዚህ ሕይወት ግባችን አላህን ማስደሰትና ለመጨረሻው ዓለም መዘጋጀት መሆን አለበት። ይህ ዓለም ጊዜያዊ ምዕራፍ ብቻ ነው። ስለዚህም በጥበብ ልንጠቀምበት፣ ራሳችንን ለማሻሻልና ሌሎችን ለመርዳት ልንጥር ይገባል። ይህም በዚህኛ ዓለምም ይሁን በዚያኛው ዓለም ከስኬታማዎቹ እንድንሆን ያስችለናል።

ሞት መሸሽ የማንችለው እውነት ነው። በሕይወታችን ውስጥ ያለው ግባችን አላህን ብቻ ማምለክ፣ መልካም ስራዎችን መስራት እና የተከለከሉ ነገሮችን መራቅ ነው። እጣ ፈንታችን አሁን በምንሰራቸው ተግባራት ላይ የተመሰረተ ነው። ስለዚህም የገነትን ደስታ ለማረጋገጥ ይህንን እድል ወይ እንጠቀምበታለን። ወይም ችላ ብለን ራሳችንን በጀሀነም ቅጣት እንጎዳለን።

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦ "እውነተኞቹ ምእመናን በእርግጥ በድሎት ውስጥ ናቸው። ከሓዲዎቹም በእርግጥ በገሀነም ውስጥ ናቸው።"

ቁርኣን 82:13-14

Part of the

مركز المعلومات الإسلامي
Islamic Information Center
للتعريف بالإسلام

# ISLAMIC e-LIBRARY

Learn more about Islam with our informative and educational materials, translated to over 50+ languages

Quran
Flyers
Books

iicdxb.com/flyers

@islamicicdxb